21ኛ ዓመት ቁጥር 1
21th Year No. 1

ባሕር ዳር ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም
Bahir Dar, 03 February, 2016

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ.91.91ብር
Unit Price Birr 91.91

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ

Content

Proclamation No. 230/2015
The Amhara National Reginal State Executive Organs Re-Establishment and Determination of their Powers and Duties Proclamtion

## አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም፣ ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ከመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ክንውን ማግስት በሀገሪቱ የተቀረፀውን ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማሳካቱ ረገድ ክልሉ የሚኖረውን ድርሻ በዓይነትም ሆነ በመጠን ከፍ ለማድረግና የህዝቡን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተቃኘ መንግስታዊ አደረጃጀት መፍጠርና በአዲስ መንፈስ ወደ ስራ መግባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 230/2015

### A Proclamation Issued to Provide for the Re-Establishment, Organization and Determination of their Powers and Duties of the Amhara National Regional State Executive Organs

WHERE AS, it has been necessary to create a Government structure oriented with developmental and democratic outlook, and enter in to a renewed duty with to enabling our Regional State to boost its share both in kind and quantity with respect to accomplishing the first growth and transformation plan formulated at the national level and thereby ensure the maximum benefit of the people at large thereof ;

ከዚሁ ከሁለተኛው ዕቅድ መባቻ ጋር በተያያዘ በስራ ላይ ያለውን የክልላዊ መንግስቱን አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ካዳጊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች፣ የተልዕኮ ተዛምዶ ወይም የስራ ቀረቤታ፣ ወጭ ቆጣቢነትና ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግስት አካላት ጋር ሊኖር የሚገባውን ተናቦ የመስራት ፋይዳ ታሳቢ አድርጎ እንደገና በመቃኘትና ዝርዝር የስራ ድልድላቸውን በመከለስ ተገቢውን ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ይህንኑ መነሻ በማድረግ ተያያዥነት ያላቸውን የስራ ዘርፎች እያሰባሰቡ በአንድ አስፈፃሚ አካል ስር ከማጠቃለል ጐን ለጐን ዓላማ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ለልማቱ መፋጠን ባላቸው ተጨባጭ እርባና ላይ በመመስረት አበይት የትኩረት መስኮቻቸውን ከወዲሁ ለይተው ይበልጥ በነዚሁ ላይ እንዲረባረቡና ለውጤታማ አፈፃፀም እንዲተጉ የሚያስችላቸውን ህጋዊ ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከነዚሁ ቁልፍ መርሆዎች ጋር በተያያዘ ቀድሞውኑ ከተቋቋሙበት ተልዕኮ ጋር የተገናዘበ የተግባርና ሀላፊነት ሽግሽግም ሆነ የተጠሪነት ለውጥ ሊደረግባቸው የሚገቡትን የክልሉን አስፈፃሚ አካላት በውል ለይቶና ሁኔታው በፈቀደ መጠን አደረጃጀቶቻቸውን ከተሻሻለው የፌደራሉ መንግስት አወቃቀር ጋር አጣጥሞ በግልፅ መደንገግና ለሀገራዊው የጋራ ግብ ስኬት እርስ በርስ የሚደጋገፉበትን የተሳለጠ እና ተመጋጋቢ የአሰራር ስርዓት ማስፈን እንደሚገባ በመታመኑ፤

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ /49/ ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

WHERE AS, taking this account second growth and transformation plan in practice Regional state executive organs Re-establishment and Determination focus on growth flexible opportunities, mission or related work save expense with structure of the Federal Government and thereby create a speedy system in which they would support each other, failing an exaggerated cost;

WHERE AS, taking this into account, besides collecting interrelated activities and organize them under one executive body , it has been appropriate to put in place an enabling legal atmosphere where by executive organs identify their main operational areas od strategic importance and strive more on these areas towards achieving effective performance on the basis of underlined significance for the acceleration of the development thereof ;

WHERE AS, having adhered to these key principles and taken into consideration the positive results obtained and multi furious tendencies observed during the study, findings and implementation of the business process Re-engineering conducted by the Regional state, it is believed that a need has arisen for the proper identification of those executive organs requiring a shift of duties and responsibilities or a change of accountability in conformity with their establishment objectives as well as clearly provide for the legislation of their organizational set up possibly harmonizing with structure of the federal Government and thereby create a speedy system in which they would support each other failing an exaggerated cost;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with the powers Vested in it under Article /49/ sub Articles 3/1/ of the revised Constitution of the National Regional State hereby issued this proclamation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) **"ቢሮ"** ማለት በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ህግ የተቋቋመና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆነ የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ነው፤

2) **"የቢሮ ኃላፊ"** ማለት የዚሁ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሆኖ እንዲያገለግል በህገ-መንግስቱ መሰረት የተሾመ ወይም የሚሾም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

3) **"ምክር ቤት"** ማለት የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን እንደተገቢነቱ የየርከኑን አስተዳደር ምክር ቤቶች ሊጨምር ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

### 3. ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /60/ ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

## PARTE ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "the Amhara National Regional State Executive Organs Re establishment, Organization and Determination of their powers and duties proclamation No.230/2015''

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise in this proclamation :

1) "**Bureau**" shall mean an executive office established or to be established as per this proclamation or any other laws and having become member of the Council of Regional Government thereof ;

2) "Bureau Head" shall mean any natural person appointed or to be appointed to serve in such an executive office pursuant to the provisions of the constitution;

3) "Council" shall mean the council of the National Regional Government which may as appropriate, include those administrative councils at various levels.

## PART TWO
## THE HEAD OF GOVERNMENT, DEPUTY HEAD OF GOVERNMENT AND THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT

### 3. Powers and Duties of the Head of Government

The powers and duties of the Herad of Government of the Amhara National Regional State shall be those stipulated under the provisions of Art. /60/of the Revised Regional Constitution.

## 4. ስለ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /61/ ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 5. ስለ ምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር በብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /58/ ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 6. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ርዕሰ መስተዳድሩ፤

ለ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /10/ ሥር የተመለከቱትን ቢሮዎች የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎች፤

መ/ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣናት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ /1/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ድንጋጌ ሥር የተመለከተው የትኛውም የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ በጽሁፍ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ይሣተፋል፡፡



## 4. Powers and Duties of the Deputy Head of Government

The powers and duties of the Deputy Head of Government of the Amhara National Regional State shall be those stipulated under the provisions of Art. /61/ of the revised Regional Constitution.

## 5. Powers and Duties of the Council

The powers and duties of the council of the Amhara National Regional Government shall be those stipulated under the provision of Art. /58/ of the Revised Regional Constitution.

## 6. Members of the Council of the Regional Government

1) The Council of the Regional Government shall have the following members as bellow:

a/ The Head of Government;

b/ The Deputy Head of Government;

c/ Those superintendents in charge of the Bureaus as are enumerated under Art. /10/ of this proclamation hereof ;

d/ Other officials to be designated by the Head of Government based on the proclamation.

2) Whenever any one of the Bureau Heads indicated under Sub-Art 1/c/ of this Article hereof , is unable to attend sessions of the council, the Deputy Bureau Head having seniority in appointment, shall so participate in such sessions provided that no other delegations have been conferred before in writing on exceptional grounds.

## 7. ስለ ክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /62/ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ሥር የተመለከተው የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ይሆናል፤

2) የጽ/ቤቱ ኃላፊ በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የሚሾም ሆኖ፡-
   ሀ/ የምክር ቤቱን ጉዳዩች በበላይነት ያስፈጽማል፤
   ለ/ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ያለ ድምፅ ይሣተፋል፣ ሃሣብና አስተያየትም ይሰጣል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ሥር የተደነገገው ለበታች የአስተዳደር ጽ/ቤቶችም ሆነ ኃላፊዎቻቸው በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 8. ስለ ምክር ቤቱ የመሰብሰቢያ ጊዜ፣ የስብሰባ ስነ-ሥርዓትና አመራር

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት፡-
   ሀ/ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤
   ለ/ ምልአተ-ጉባኤ የሚሆነው ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ሲገኙ ይሆናል፤
   ሐ/ ምክር ቤቱ ውሣኔዎችን የሚያሣልፈው በተባበረ ድምፅ ይሆናል፤ በተባባረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ ግን ጉዳዩ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፡፡

## 7. Office of the Council of the Regional Government

1) The office of the Council of the Regional Government shall be that office of the Head of Government indicated under the provisions of Art/62/ sub art/2/ of the Revised Regional constitution;

2) To be appointed with the rank of a Bureau Head hereof the Head of the office shall:
   a/ direct over the execution on the cabinet affairs;
   b/ attend without vote, the cabinet session as well as render suggestions and opinions.

3) The provisions of sub-art/1/ and /2/ of this article hereof shall, mutatis mutandis apply to the subordinate administrative offices their respective Head.

## 8. Meeting Time Procedure And Chairing

1) The Council of the Regional Government shall:
   a/ with the details shall be specified in a regulation undertake ordinary and extra ordinay sessions;
   b/ the constitution of a quorum in this regard shall require the presence of more than half its members at meeting;
   c/ its decisions shall be passed by consensus, provided that they may be taken by a majority vote in default of same.

2) የምክር ቤቱ አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፡-

ሀ/ ለምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ ሆነው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ/ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፤

ሐ/ ለምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ የቀረበ ማናቸውም ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በኩል መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፡፡

3) ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

## 9. ስለ ምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ይረዱት ዘንድ የሚቋቋሙ የየምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፤

2) የእነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለ ቢሮዎች በጠቅላላው

## 10.ስለ መቋቋም

የሚከተሉት ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1) ግብርና ቢሮ፤

2) ንግድ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ፤

3) ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ፤



2) Without prejudice to the rights of the members of the Council of the Regional Government to submit an agenda, the Head of Government shall:

a/ decide on the agenda qualifying for the referred to the council;

b/ preside over the councils meeting;

c/ postpone the meeting for some future proceeding in case he has found out that a given agenda is subject for consideration by the standing committee of the council concerned.

3) In the absence of the Head of Government, the deputy Head of Government shall, in his place, preside over the meetings of the council.

## 9. Standing Committees of the Council

1) The council of the regional government shall have established various standing committees comprising council members with the view to assisting discharge its responsibilities;

2) The powers and duties of the standing committees shall be specified by a directive of the council to be issued after wards.

## PART THREE
## THE BUREAUS IN GENERAL

## 10. Establishment

The following bureaus are hereby established by this proclamation:

1) Agriculture Bureau;

2) Trade, Industry and Market Development Bureau;

3) Urban Development, Houses and Construction Bureau;

4) ውሀ፣ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ፤
5) የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ፤
6) የቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፤
7) የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ፤
8) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ፤
9) ትምህርት ቢሮ፤
10) ጤና ጥበቃ ቢሮ፤
11) ፍትህ ቢሮ፤
12) አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ፤
13) ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤
14) የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ፤
15) የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤
16) የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፤
17) የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ።

11. <u>የቢሮዎች የወል ስልጣንና ተግባር</u>

1) እያንዳንዱ ቢሮ በየሥራው መስክ፡-

ሀ/ የፌደራሉን መንግሥት ፖሊሲዎች መሠረት ያደረጉና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን፣ስትራቴጅዎችንና ህጋጋትን ያመነጫል፣ የሥራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የክልሉንና የፌዴራሉን መንግስታት ህጐችና ደንቦች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ለሚለከታቸው ያሰራጫል፤

4) Water, irrigation and Energy Development Bureau;
5) Road and Transport Bureau;
6) Technic-Vocation and Enterprises Development Bureau;
7) Tural Land Administration and Use Bureau;
8) Finance and Economic Cooperation Bureau;
9) Education Bureau;
10) Health Bureau;
11) Justice Bureau;
12) Administrative and Security Affairs Bureau;
13) Culture and Tourism Bureau;
14) Women’s and Childrens’s affairs Bureau;
15) Labor and Social Affairs Bureau;
16) Civil Service and Human Resource Development Bureau;
17) Youth’s and Sport Affairs Bureau.

11. **<u>Collective Powers and Duties of the Bureaus</u>**

1) Each and every bureau shall in connection with its sphere of activities:

a/ initiate regional policies, strategies and laws based on those policies of the Federal Government and having due regard to the objective realities of the regional state ,as well as prepare work plan along with the budget proposal and implement same upon approval;

b/ implement the federal and regional laws and regulations throghout the regiona state;

c/ perform the study and research activities; collect, compile and analyze information , and distribute same to the pertinent bodies;

መ/ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ የራሱን የበታች አደረጃጀቶች ይፈጥራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ መሰል አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡለትም ለብሄረሰብና ለወረዳ አስተዳደሮች ተገቢውን ድጋፍና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

ሠ/ ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ዝርዝር የማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፤

ረ/ በህግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ስምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሣል፣ ይከሰሳል፤

ሰ/ ለየስራ ዘርፉ ባለው ተገቢነት ላይ አተኩሮ የሴቶችን፣የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንንና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ህገ-መንግስታዊ እኩልነት፣ ሙሉ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የነዚህኑ ህብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ በዕቅድ አካቶ ይሠራል፡፡

2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ /31/ ወይም በየማቋቋሚያ ህጐቻቸው በተደነገገው መሠረት ተጠሪዎች የተደረጉለትን አስፈፃሚ አካላት አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ አደረጃጀቶቻቸውንና የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን መርምሮ ለሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት እንዲቀርቡ ይወስናል፤

3) ተጠሪ የተደረገለት ሌላ የክልሉ መንግስት ተቋም ወይም ድርጅት ቢኖር ይህንኑ በህግ መሠረት ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

d/ create , as may be necessary its subordinate structures throughout the regional state , follow up and monitor their activities , as well as, provide the appropriate support and advisory services to the nationality zone and woreda administrations when requested to assist them in the establishment of their own similar structures;

e/ may issue detailed implementation directives in relation to its own powers and duties;

f/ enter into contracts pursuant to law ,own property , conclude agreements, sue and be sued in its own name;

g/ emphasize on the appropriate sector to the work that shall ensure enabling constitutional equality, full participation and use of the women , disabled persons, elders and to those persons who are susceptible to social and economical problems; and work for these persons by mainstreaming their issue in the plan ;

2) It shall direct the overall implementation of the executive organs made accountable to it pursuant to the provisions of Article /31/ of this proclamation or their respective establishment laws; coordinate their efforts, as well as, examine their structural set ups and operational programs prior to the decision that such be submitted for approval to the pertinent body of the regional government;

3) It shall follow up , support and supervise based on the law if there is other regional government institution or enterprise , accountable to it;

ይቆጣጠራል፡፡

4) በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጐች የተሰጡትን ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

5) ስለ ሥራው ክንውን ለርዕሰ መስተዳድሩና ለምክር ቤቱ ወቅታዊ ዘገባዎችን ያቀርባል፡፡

## 12.የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተግባር

እያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ፡-

1) ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለምክር ቤቱ ይሆናል፤

2) የሚመራውን ቢሮ ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባራቱን በሥራ ላይ ያውላል፤

3) ለቢሮው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

4) በቢሮው ውስጥ ውጤታማ የሥራ አመራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፡፡

## 13.የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተግባር

1) እያንዳንዱ ምክትል የቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሚመለከተው ቢሮ ኃላፊ ሆኖ በዚሁ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2) የቢሮ ኃላፊው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል፤

3) በማናቸውም ቢሮ ውስጥ የሥራው መጠንና ውስብስብነት ከመጠየቁ የተነሣ ከአንድ በላይ የሆኑ ምክትሎች በሚገኙበት ጊዜ የቢሮ ኃላፊው በተለይ የጹሁፍ ውክልና የሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር እርሱን ተክቶ ቢሮውን የሚመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል የቢሮ ኃላፊ ይሆናል፡፡

4) It shall implement the specific powers and duties as are provided for it in this proclamation and other laws;

5) It shall submit periodice reports to the Head and council of the regional government in respect of the performance of its duties.

## 12. Accountability and Duty of the Bureau Heads

Each and every bureau head shall :

1) Be accountable to the Head and council of the Regional Government;

2) Represent the Bureau under his/ her leadership and implement its powers and duties;

3) Effect expenditures in accordance with the work program and budget approved for the Bureau;

4) Put in place an effective management system for the Bureau and follow up its observance thereof;

## 13. Accountability and Duty of the Deputy Bureau Heads

1) Each and every Deputy Bureau Head shall, being accountable to the Bureau Had concerned, carry out such duties as are specifically assigned to him / her by this Head;

2) He or she shall replace and act on behalf of the Bureau in the absence and inability of the Bureau Head to carry out the tasks ;

3) Where more than one Deputy are present in any given Bureau due to the volume and complexity of the work, the Deputy Bureau Head senior in appointment, shall direct the Bureau in the absence of the bureau Head, unless it is ascertained that the latter has specifically delegated another person to replace him in Writing.

## ክፍል አራት

## ስለ ቢሮዎች ዝርዝር ስልጣንና ተግባር

### 14. የግብርና ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ግብርና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱን የግብርና መር ፖሊሲና ስትራቴጅ መሠረት ያደረገ የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂዊ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ይፈጽማል፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

2) ለአርሶ አደሩ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ ለምርምር አገልግሎት የመነሻ ሀሣብ ይሰጣል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

3) የሰብልና የእንስሳት በሽታዎችን፣ ፀረ-ሰብል ተባዮችንና አረሞችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የማቴሪያልና የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፤

4) በምርምር የተገኙ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ያቀርባል፣ ያላምዳል፣ ፕሮቶታይፖችን ያመርታል፣ ለሚያመርቱትም ያሰራጫል፣ የገጠር መካይናዜሽንን ያስፋፋል፤

5) በግብርናው ዘርፍ መዋዕለ-ንዋያቸውን ማፍሰስ ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች ተገቢውን መረጃና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

6) በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ መስክ ለአርሶ አደሩና በግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ስለአጠባበቅ፣ አያያዝና አጠቃቀሙ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የልማቱን፣ የጥበቃውንና አጠቃቀሙን ሁኔታ በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

## PART FOUR

## Specific Powers and Duties of the Bureaus

### 14. The Bureau of Agriculture

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Agriculture shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1. Prepare and implement the short, medium and long term strategic plans and programs as well as cause the promotion of a rapid and sustainable agriculture;
2. Avail Extension service and technical support to the farmers, render initial proposal for research purpose and follow up their effective application thereof;
3. Provide material and technical support with the view to preventing and contolling crops' and animals diseases as well as anti harvest pests and weeds;
4. Introduce and adapt new technological findings obtained by research, produce prototypes and disseminate same to potential producers;
5. Provide the appropriate information and advisory services to private properietors wishing to invest their capital in the agricultural sector;
6. Render educational, training and counseling services to the farmers and private investors engaged in the agricultural sector as regards the development, protection and use of the natural resources, follow up and supervise over the development, protection and utilization of same thereof;

7) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአርሶ አደሩ የብድር አገልግሎት የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

8) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በገጠሩ አካባቢ የስራ ዕድል ፈጠራን አስመልክቶ ወጣቶች በዘመናዊ የግብርና ልማት ተሰማርተው በብቃት የሚሳተፉበትንና በልዩ ትኩረት የሚደገፉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

9) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የውሀ እቀባና የአነስተኛ መስኖ ልማት ስራዎችን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ አነስተኛ የመስኖ አውታሮችን በተመለከተ የግንባታና የጥገና ስራዎችን ያካሂዳል፣ የባህላዊ ወንዝ ጠለፋ ስራዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

10) የግብርና ግብዓቶች ጥራታቸው ተጠብቆ ለተጠቃሚዎች መሰራጨታቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

11) የግብርና ልማቱን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጅዎችን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ተቋማትንና መሰል ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፤

12) በግብርና ልማቱ ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸውን ወቅታዊ ሁኔታዎች ይከታተላል፣

ይገመግማል፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የምግብ ዋስትና ስራውን ይቆጣጠራል፡፡

13) በታቀደ አኳሀን የሚፈፀሙ የህዝብ ሰፈራ መርሀ-ግብሮችን በማስፈጸም ረገድ አግባብነት ያላቸውን ወረዳዎች የስራ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

7) Create in collaboration with the appropriate bodies favorable conditions whereby farmers may be provided with credit facilities;

8) Create a favourable condition , in collaboration with the pertinent bodies concerning to job opportunity in rural area for youths,operate in modernized development of agriculture, participate efficiently and shall be supported with a special attention;

9) carry out water harnessing and the small scale irrigation development activities cause to be conducted in same; carry out construction and maintenance activities concerning to the small scale irrigation infrastructures; encourage the expansion of traditional river diversion activities and provide support thereof ;

10) follow up and supervise over the distribution of agricultural inputs in a desired quality;

11) establish, organize and direct training institutions and related centers assisting the acceleration of the agricultural development and improvement of the reural technologies;

12) follow up and evaluate the periodic conditions likely to impact on the agricultural development, put an early warning system in place, as well as, monitor the food security activities;

13) coordinate and support the appropriate woredas regarding the implementation of their re-settlement programs of the people shall be executed;

## 15.የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው ማናቸውም የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ የንግድ ፖሊሲ፣ ህግና ደንብ መሰረት መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊነት ያለውና ስነ-ምግባር የተላበሰ የንግድ አሰራር እንዲከበር ያደርጋል፣ ህገ-ወጥ የንግድ አሰራሮችን ይከላከላል፤
2) የሀገሪቱን የንግድና ኢንዱስትሪ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የንግድና ኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ የጥናት፣ የስልጠና፣የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል አካላት ጋር በመተባበር በዘርፉ የሚታዩ ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤
3) በክልሉ ውስጥ በንግድ ሥራ የሚሰማሩትን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በንግድ ህጉ መሠረት ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤
4) በክልሉ ውስጥ በትርፍ ስራ ላይ የተመሰረተ ዓላማ ይዘው የሚንቀሣቀሱ የንግድ ማህበራትን መመስረቻ ጹሁፎች፣ መተዳደሪያ ደንቦችና የእነዚህኑ ማሻሻያዎች ተቀብሎ በመመርመርና ህጋዊነታቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤
5) የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ የነጋዴዎችን የተሟላ መረጃ ይይዛል፤

## 15. Trade, Industry and Market Development Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Trade Industry and Market Developments shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties;

1) Follow up and supervise the conduct of trade activities undertaken in the regional state pursuant to the national policies, laws and regulations, cause the observance of lawful and ethical trade activities and prevent the undertaking of those activities in an illegal manner;
2) Encourage the promotion of trade institution in the Regional State on the basis of the country's trade and investment policies and strategies, render the study, training, technical and advisory services and cause the resolutions of outstanding difficulties in the sector through follow up of same in collaboration with the pertinent federal and regional bodies;
3) Register, pursuant to the commercial laws, issue and renew licence to those domestic investors engaged in trade activities throughout the regional state as well as collect the appropriate service fees.
4) Register by investigating and assuring its legality of the submitted by-laws, regulations and their own revisions of the trade societies who perform based on the objective of profit making trade in the region;
5) Establish and administer the regional book of trade and thereby maintain the complete profile of the traders therein;

6) የገበያና የንግድ ሥራ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመተንተንና በማሰራጨት ረገድ ተፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲኖር ያደርጋል፤

7) የግብይት ልማት ዘርፉን ለማጠናከር በተመረጡ መስኮች ለክልሉ የግብይት ተዋንያ የብድር አገልግሎት ያመቻቻል፤

8) በክልሉ ውስጥ የንግድና ዘርፍ ማህበራት እንዲሁም የእነዚሁ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ በንግድ አሰራር ረገድ ያላቸው ግንዛቤና ተሳትፎ እንዲዳብር ያደርጋል፤

9) በጠቅላላ የጥራት አሰራርና አስተዳደር እንዲሁም በድርጅቶች መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የስራ ቁርኝት አሰራር ያስተዋውቃል፤

10) የክልሉን ምርቶችና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሚረዱ ቋሚ ኢግዚቢሽኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ለሚያዘጋጁ አካላት ድጋፍና ፈቃድ ይሰጣል፣ በሌሎች ክልሎች ኢግዚቢሽኖች ላይ ይሳተፋል፤

11) የዋና ዋና የግብርና ምርቶችና ግብይቶች የገበያ ፍላጐት ትንበያ ጥናት ያካሄዳል፣ ይቆጣጠራል፤

12) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የግብይት አማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

13) የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርቡበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤

6) Provide the necessary support with regard to the collection, compilation analysis and distribution of market and business related information and thereby cause the creation of marketing ties;

7) Facilitate the credit service for the regional marketers to strengthen the market development sector being selected;

8) Encourage and support the establishment in the Regional state of business and sectoral associations and their respective councils as well as promote their awareness and participation in respect of business procedures;

9) Promote general quality operation and management as well as working ties to be forged between and among enterprises on the basis of contractual agreements;

10) Cause the preparation of exhibitions, where by the Regionl products and services might be displayed, render support and license to those bodies preparing same and participate in such exhibitions are organized by other regional states;

11) Undertake and monitor market demand forecast studies with regard to those major agricultural products and inputs;

12) Facilitate in collaboration with pertinent bodies of issue, conditions for the creation and strengthening of market centers for agricultural products; establish and thereby support marketing advisory council;

13) Set up and follow up system where by agricultural and industrial outputs may be offered for marketing with their quality standard having been maintained thereto ;

14) የግብርና ምርቶች አቅርቦትና በገበያ ረገድ ያላቸው ቀጣይነት አስተማማኝ ይሆን ዘንድ በተለይ በኮንትራት የማምረት ስርዓት እንዲስፋፋ ያበረታታል፤

15) የኢንዱስትሪ ተቋማትን የማምረት አቅም ለማሣደግ ይሠራል፣ የፋይናንስ፣ የትራንስፖርትና ትራንዚት አገልግሎት እንዲያገኙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

16) ከክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሀሣቦችን በየጊዜው እያመነጨ ሊጠኑና በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን በመለየት አግባብ ላለው የፌደራል መንግስት አካል ያስተላልፋል፣ በክልሉ አቅም ሊፈፀሙ የሚችሉት ደግሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

17) የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን በመደገፍ ረገድ ቁልፍ ሚና ካላቸው የክልሉና የፌደራሉ አስፈፃሚ አካላትም ሆነ የከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት ጋር የጋራ ዕቅዶችን አውጥቶ ይሰራል፤

18) በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ባለሃብቶች በተሸጋገሩበት ዘርፍ እድገታቸው እንዲፋጠን ለማድረግ የማምረቻ ቦታና የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንዲሟላላቸው ይሰራል፣ በፕሮጀክት ዝግጅትም ሆነ በአዋጭነት ጥናት ረገድ ይደግፋል፤

19) የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ያስፋፋል፣ በክልሉ ውስጥ የኢንዱስትሪ መንደሮችን ያደራጃል፣ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

14) Encourage the expansion of productive system by contract so that there shall be a reliable supply of agricultural products and sustainable marketing thereof;

15) Strive towards the promotion of productive capacity of industry institutions and support same in order that they shall be provided with the financial, transport and transit facilities;

16) Having, from time to time initiated industrial project ideas on the basis of the country's investment policies and law, duly identify those requiring examination and implementation and convey to the pertinent body of the federal Government as well as cause the implementation of those projects capable of being materialized with the capacity of the region, in collaboration with the regional investment commission;

17) Work for by issuing communal plans with the regional and federal executive bodies, as well as, with the higher education and research institutions that have a great contribtion, with regard to support manufacturing sector;

18) Work for investors transferring from small to medium level having the production place and infrastructure development service to be fullfiled , in order to speed up their growth with the transferring sector , by industry manufacturing sector;

19) Expand rural industrialization , organize industrial areas in the region , and cause the infrastructure to be fulfilled ;

20) የንግድ ስርዓቱንና ሸማቹን ህብረተሰብ የሚጐዱ የተለያዩ ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣ አስተዳደራዊና ህጋዊ ርምጃዎችን ይወስዳል፤

21) የሸማቹን መብት ለማስከበር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችንና ለነዚሁ ሲባል የሚፈጠሩ አደረጃጀቶችን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤

22) ከንግድ አሰራርና ሸማቾች መብት ጋር በተያያዘ ሊፈፀሙ የሚችሉ ወንጀሎችንና ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮችን የሚከታተል የራሱን ዐቃቤ ህግ የስራ ክፍል ያደራጃል፤

23) በንግድ ውድድርና በሸማቾች መብት አጠባበቅ ረገድ የሚነሱ አለመግባባቶች በድርድር ወይም በእርቅ እንዲፈቱ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

24) ህገ-ወጥ የንግድ አሰራሮችን ለመቆጣጠርም ሆነ ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመመርመርና የሚወስዳቸውን አስተዳደራዊ ርምጃዎች ለማስፈፀም እንዲሁም ለምስክሮች መጥሪያ ለማድረስ የክልሉን የፖሊስ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፤

25) ከንግድ ውድድርና የሸማቶቾች መብት አጠባበቅ አስመልክቶ የሚነሱ ፍታብሄር ነክ ጉዳዬችን ተቀብሎ የማትና የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

20) Supervise different illegal trade activities , that shall harm the trade system and the purchaser, take administrational and legal measures;

21) Support and coordinate the activities and organizations that cause to respect the purchaser's right;

22) Shall have a prosecutor that follows up crimes to be performed, that are related to trade procedure and purchaser's right and civil cases;

23) Establish work procedure that enable to resolve disagreements, which shall be raised on the trade system and purchasers rights by agreement or arbitration ;

24) To control illegal trade systems investigate crimes that shall be performed; as well as cause to implement administrational measures that it takes and addresses summon to wittnesses, may use the regional police ;

25) May establish administrational tribune that shall have a power of investigating and juding on civil cases raised by receiving same , concerning to trade competition and purchasers' rights of protection;

26) በኢፌድሪ የወንጀል ህግ፣የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት እና በሌሎች ህጐች ከንግድ አሠራርና ሸማቾች መብት ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዬችን የመመርመር፣የመክሰስ እና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የመከራከር ስልጣን ለቢሮው ተሰጥቷል፡፡

27) በንግድ አሠራር እና ሸማቾች መብት ላይ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያግዛል፣በቂ ምክንያት ሲኖረው የተመጀመረውን ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን መመሪያ ይሰጣል፣ በህገ መሠረት የወንጀል ክስ ይመሠረታል፣ያነሳል፡፡

28) አይነታቸውና የዋጋ ዝርዝራቸው በፌደራሉ የንግድ ሚኒስቴር የህዝብ ማስታወቂያ ክፍል የተገለፀው ወይም የሚገለፀው የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች በክልሉ ውስጥ ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበትና ከቦታ ቦታ ስለሚዛወሩበት ሁኔታ ይወስናል፣ እንደአስፈላጊነቱ እቃዎች ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ ለነጋዴዎች መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 16.የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱ የህንፃ ኮድ፣ የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ስራ ደረጃዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

26) The power of investigation, sue and pleading power with vested in power to the court concering to criminal cases that shall be implemented on the trade's and purchasers' right by the Ethiopan Federal Democratc Republic of the criminal law, criminal procedure code and by other laws;

27) Support investigation to be done where it believes crimes has been executed on trade procedure and purchasers' right; render directives the commencing investigation to be stopped or additional investigation to be done where it has a sufficient ground ; charge and raise the criminal case pursuant to law;

28) The trade materials and services, those which are specified or shall be specified of their lists and prices, by the Federal Trade Ministry public notice, to determine the way of their distribution, shall be selled and to transfer from place to place in the region; and ,as deemed as necessary, it may order merchants to replace where materials are finished.

## 16.The Urban Development and Construction Bureau

Wrthout prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Industry; Houses and construction shall, pursuant to this proclamation , have the following specific powers and duties:

1) Ensure the observance of the country's building codes and the standards of design and construction works in the regional State;

2) በክልሉ መንግስት በጀት ለሚገነቡ የመንግስት ኮንስትራክሽኖች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችና የኮንስትራክሽን ስራ ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

3) በክልሉ መንግስት በጀት የሚከናወኑ የመንግስት ኮንስትራክሽኖች በተገባላቸው ውል መሠረት የጥራት ደረጃቸውና የጊዜም ሆነ የዋጋ ገደቦቻቸው ተጠብቀው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል፤

4) በክልሉ ውስጥ የስራ ተቋራጮችንና አማካሪዎች ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ የቴክኒክ መገምገሚያ መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይመዝናል፣ ደረጃ ያወጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፣ የግንባታ ነክ አለመግባባቶች በሚከሰቱበት ወቅት የግልግል ስራዎችን ያከናውናል፤

5) በክልሉ ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አቅም እንዲያድግ ተፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ የግንባታ ቴክኖሎጅዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል

6) በከተሞች ውስጥ ለሚካሄደው ኢንቨስትመንትም ሆነ በከተማ ቦታና ኮንስትራክሽን ስራዎች ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፣ ተፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

7) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚደነገግ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ዕድገት በየጊዜው እያጠና የደረጃ ሽግግር እንዲደረግላቸው ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሃሣብ ያቀርባል፣ የልማት ማዕከላት እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣ የከተማ አሰፋፈርና የዕድገት አቅጣጫውን ያጠናል፣ ይከታተላል፤

2) Cause the preparation of designs and contractual documents necessary for the construction of public builidings financed by the regional government;

3) Supervise that the execution of government constructions undertaken by the budget of the regional state is in conformity with the quality standards, time as well as cost limits, as provided in their contract;

4) Register contractors and advisors in the region; render certification of professional competency; prepare standards of technical evaluation; evaluater their implementation; issue a standard, delele their licenses of necessary; perform arbitration where disagreements are appeared on the construction;

5) Perform the necessary support of the construction industry to be promoted its capacity in the Region;

6) Extend the necessary cooperation in respect of investment or urban land and construction activities undertaken in urban center; and render the necessary support of same;

7) The particulars shall be stipulated with regulation, to be issued, for the implementation of this proclamation; study from time to time , the growth of urban centers found in the regional state and thereby propose their standardized promotion to the Regional Government council; render an all-out and integrated support for their transformation into development centers, as well as, study and follow up the urban settlement and its development directions;

8) በከተሞች ውስጥ የያንዳንዱን ከተማ መሪ ፕላን የጠበቁ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚስፋፉበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

9) የክልሉ ከተሞች ውብ፣ ፅዱና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮም ሆነ ለሥራ ተስማሚና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤

10) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የከተማ አስተዳደሮች በእቅድና በከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አፈጻጸም ረገድ ይከታተላል፣ይደግፋል፣ ጥያቄ ሲቀርብለትም የገጠር ቀበሌ ማዕከላትንና የከተሞችን ፕላን ያዘጋጃል፣ ስራውን በበላይነት ይመራል፤

11) በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን የኮንስትራክሽን፣ የከተማ ልማትና ቤት ነክ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ይነድፋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

12) የግል ሴክተሩን አቅም በማሳደግ ዘርፉ በከተማ ልማት፣ በሪል-ስቴት ስራዎችና በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች በንቃት የሚሳተፍበትን ስልት ይቀይሣል፤

13) የከተሞችን ልማት ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያግዙ የተለያዩ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

14) የክልሉ ከተሞች ሁሉን አቀፍ በሆነ ደረጃ የሚጠቀሙባቸውን ልዩ ልዩ ረቂቅ የህግ ማዕቀፎች ያዘጋጃል፣ የዕድገት ደረጃቸውን በጠበቀ መንገድ እንዲሻሻሉ ያደርጋል፤

15) ከተሞች ከአጋር አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩባቸውን ስልቶች በመቀየስ ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት የሚጠናከርበትን ዘዴ ይቀይሣል፤

8) Devise a mechanism through which infrastructures are to be expanded in urban centers in compliance with the master plan of each city, as well as, closely follow up and support therof;

9) Provide the necessary support and assistance with view to turning the urban centers of the regional state become attractive, clean, and green, as well as, competitive and comfortable either for habitation or work;

10) Follow up and support the urban administration of the Regional State interms of planning and urban palan preparation, and prepare plans for those rural kebele and urban centers upon request and direct over such activities thereof;

11) Formulate the construction, urban development and housing policies and strategies applicable to the Regional State and implement same upon approval;

12) Having enhanced its capacity , devise a mechanism through which the private sector shall be able to participate attentively in urban development activities;

13) Conduct various studies which might be instrumental to speed up the development of urban centers and realize good governance and carry out capacity building activities, and cause to be studied in same with others;

14) Prepare a variety of draft legislative frameworks to be used by the regional cities in an all – embracing manner; and cause their amendments as per the level of in same development;

15) Devise a mechanism through which decentralized administration system might be strengthened by figuring out strategies in which urban centers shall work in collaboration with the partner bodies thereof;

16) የከተማ መሬት ወጭ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

17) የከተሞችን ልማት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንዲደራጁ ለክልሉ መንግስት ጥያቄ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

18) የኢንቨስትመንት ስራዎችን ጨምሮ ለተለያዩ የልማት አገልግሎቶች የሚውል መሬት በበቂ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያሰጣጡንም ፍትሀዊነት ይከታተላል፤

19) በክልሉ መንግስትና በከተማ አስተዳደሮች ባለቤትነት ስር የሚገኙ ቤቶችን በሚመለከት አግባብ ላላቸው አካላት ተፈላጊውን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ያደርጋል፤

20) የከተማው ነዋሪ ህዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ መኖሪያ ቤቶችን ሰርቶ ይጠቀም ዘንድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ያደርጋል፡፡

16) Put various working procedures in place so that urban land might be utilized in an economic and effective manner, as well as, follow up and supervise their implementation;

17) Propose to the Regional government as to the organization of those institutions vital for the promotion of urban development and implement same upon approval;

18) Cause to the preparation of sufficient land to be set aside for various development services, including investment efforts, and follow up the fairness of its delivery thereof;

19) Provide technical and administrative support necessary for the appropriate bodies as regards those houses under the ownership of the Regional Government and urban administrations;

20) Cause the facilitation of conditions enabling the inhabitants of the urban centers to build dwelling houses comparable to their descent capacity and benefit therefrom;

## 17. <u>የውሀ፣ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ውሀ፣ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉን የውኃ ሀብት መረጃዎች በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለልማት ሥራዎች ያውላል፣ እንዲውሉ ያደርጋል፤

2) የክልሉን የውኃ ሀብት ክምችትና ስርጭት ያጠናል፣ እንዲጠና ያደርጋል፣ ያስተዋውቃል፤

## 17. **<u>The Water, Irrigation and Energy Development Bureau</u>**

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the regional water, rrigation and energy development bureau shall, pursuant to this proclamation , have the following particular powers and duties:

1. Having collected, organized and analyzed the data with regard to the regional water resource, employ or cause the employment of same for developmental activities;
2. Study the regional reserves of water resource and its distribution, cause same to be studied and promote thereof;

3) የክልሉን የውኃ ሀብት ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

4) የክልሉን ውኃ ሀብት ለማልማትና በጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

5) የክልሉ የውኃ አካላትና ተቋማት ከብክለትና ከአደጋ ስለሚጠበቁበት ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

6) በክልሉ መንግስት አማካኝነት የተገነቡ የመስኖ ግድቦችን፣ በዩችንና ሌሎች አውታሮችን ተረክቦ ያስተዳድራል፣ ይንከባከባል፣ ይጠግናል፣ ስለአጠቃቀማቸውም ዝርዝር የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፤

7) በፌደራሉ መንግስት አማካኝነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የውኃ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን በባለቤትነት ድጋፍ ያደርጋል፤

8) በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ንፁህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋንን ለማሳደግ የአዳዲስ ጥናትና ዲዛይን የማሻሻያና የማስፋፊያ ሥራዎች እንዲካሄዱና ግንባታቸው እንዲከናወን ያደርጋል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፤

9) በከተማና በገጠር አካባቢዎች ለንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት የተገነቡ ተቋማት ዘላቂና አስተማማኝ አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዲኖራቸው ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣል፤



3. Devise mechanisms enavling to utilize the regional water resource in a sustainable and reliable way and follow up their implementation;

4. Deliver licensing services with the view to developing and putting to use the regional water resource and follow up the implementation thereof;

5. Work in collaboration with the parties pertinent to the issue on the protection, from pollution and other damages of the water bodies and institutions in the regional state;

6. Administer,care and maintain by receiving the constructed irrigation dams, drainages and other infrastructures with regard to the regional government, and establish particular work procedure system of their use;

7. Render support with a status of ownerhip in respect of water development projects carried out in the regional state under the auspices of the federal Government;

8. With the view to promoting the supply of potable water both in urban and rural areas, cause the undertaking of newer study, design, improvement and expansion works as well as construction thereof and carry out the appropriate follow up and supervise therewith;

9. Render professional support to enable potable water supply, facilities constructed in urban and rural areas so that they would provide sustainable and reliable service;

10) በክልሉ ውስጥ ወጥነትና ፍትሃዊነት ያለው የውሃ ታሪፍ፣ ሮያልቲና የወጪ አመላለስና አወሳሰን ስርዓት ቀርጾ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ይህንኑ አስመልክቶ በየጊዜው ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

11) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የመስኖና የገጠር መጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያደራጃል፣ ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

12) የክልሉን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል፣ በሌሎች ያሠራል፣ ግንባታቸው ጥራቱን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፤

13) በመስኖ ልማት ሥራዎች ለሚሳተፉ አጋር አካላት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

14) የተገነቡ የውኃ ተቋማት ዘላቂና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የከፍተኛና መለስተኛ ጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

15) ከውኃ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ስንታዳርዳቸውን ያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስርጭት እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያበረታታል፤



10) formulate a uniform and equitable water tariff, royalty, as well as, cost-recovery and determination system in the regional state, submit to the council of the government of the region and cause its implementation upon approval, carry out periodic studies and cause such studies to be undertaken by others;

11. organize, register, follow up and support the irrigation and the rural potable water beneficiaries associations in the region;

12) undertake study and design activities with view to utilizing the region's water resource for irrigation purposes, cause same to be undertaken by others, as well as, hand over to the consumers those construction projects having been completed as per the desired quality;

13) provide professional support for those partner bodies wishing to participate in irrigation development works and carry out the appropriate follow up and supervisory activities in an effort to make the would be constructed irrigation facilities comply with the required standards;

14) carry out high and medium –level maintenance works or cause same to be carried out so that constructed water facilities may deliver the desired and sustainable service;

15) ensure that the technologies having to do with water works meet the required quality and comply with the standards, authorize and encourage the entry of the latest ones into distribution after testing;

16) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በውኃ ሀብት ላይ የሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮችን ያካሄዳል፣ ያስተባብራል፣ የምርምር ውጤቶችንና አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በክልሉ ውስጥ ያስፋፋል፤

17) የክልሉን የውኃ ሀብትና የውኃ አቅርቦት ተቋማት በአግባቡ ለመጠበቅና ለመጠቀም የህብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜት የሚዳብሩና በዘርፉ የተሰማሩትን አካላት ክህሎት የሚያሳድጉ ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤

18) በክልሉና በፌደራሉ መንግስት አካላት የሚወጡ የውኃ ሀብት አስተዳደር ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

19) ክልል አቀፍ የሆኑ የውኃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ ህግና ደንብ ረቂቆችን፣መመሪያዎችን፣ ስትራቴጂዊ እቅዶችን፣ ስታንዳርዶችንና የስራ ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

20) በክልሉ ውስጥ የኢነርጅ ልማት እንዲስፋፋ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲጠኑ ያደርጋል፤

21) የግል ባለሃብቶች በኢነርጅ ልማት ስራዎች በስፋት እንዲሣተፉ ያነሳሳል፣ የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎችን በማከናወን ያበረታታል፤

16) in collaboration with the pertinen bodies to the issue, conduct or coordinate studies and researches undertaken on water resource and promote the research findings and newer technologies in the regional state;

17) prepare and render trainings aimed at enhancing the community's sense of ownership and raising the skills of the bodies engaged in the sector with the view to properly handling and utilizing the region's water resource and water supply facilities;

18) cause the implementation in the Regional state of the water resource management laws, regulations and directives issued by both the regional and federal government bodies;

19) prepare and distribute the Region-wise draft water resource management policy, laws, regulations, directives, strategic plans, standards and working manuals, as well as, follow up and supervise their implementation thereof;

20) conduct studies, the energy development activities to be developed in the region; and cause to be studied by others;

21) initiate private investors to participate widely in energy development activities; and encourage by performing different promotion activities;

22) በክልሉ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት በሚያስፈልገው ሜጋ ዋት መጠን ላይ አግባብ ካላቸው የፌደራሉ መንግስት አካላት ጋር ይመካከራል፣ እንደአስፈላጊነቱም የሥልጣን ውክልና ሲሰጠው ኤሌክትሪክ የማመንጨትና የማሠራጨት ሥራ ፈቃዶችን ይሠጣል፣ ይቆጣጠራል፤

23) በገጠር ኢነርጅ አቅርቦት ረገድ የተለያዩ የኢነርጅ አማራጭ ቴክኖሎጅዎች በሠርቶ ማሣያ ሙከራ ተደግፈው እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የኢነርጅ ተጠቃሚዎችና የቴክኖሎጅ አምራቾች ተደራጅተው የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

24) በክልሉ ውስጥ የማገዶ ተክል በስፋት እንዲለማና አቅርቦቱ የህብረተሰቡን ፍጆታ የበለጠ እንዲሆን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

25) የአካባቢ ጥበቃን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ሆነው ተመጣጣኝ ዋጋና ብቃት ያላቸውን የኢነርጅ ምንጮችና ቴክኖሎጅዎችን ልማት፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀምና ቁጠባ ያጣራል፣ እንደሁኔታው በግል ባለሀብቶች፣ በመንግስትና በሌሎች ዘርፎች በኩል ለህብረተሰቡ ያስተዋውቃል፤

26) ኢነርጅን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል።

## 18. የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት



22) negotiate with the appropriate federal government bodies about the necessary mega watt amount to produce the electric power in the region; as deemed as necessary, it shall render work licenses to produce and distribute electric power and supervise therein, where is rendered delegation of powers;

23) cause the development of different energy alternative technologies to be widened, supported with the test of work, with regard to the supply of rural energy, facilitate getting a credit service for energy beneficiaries and technology producers in organization;

24) cooperate and work in collaboration with the appropriate bodies the firewood to be developed and the supply of it to be more than the consumption of the society in the region;

25) investigate the energy resources and technologies development, distribution, use and save that have proportional price and be competent which consider the environment protection thereof; inform to the society with regard to private investors, public and with other sector, as deemed as, necessary;

26) collect, organize and analyse information concerning to energy, and as deemed as necessary, it shall distribute same to beneficiaries.

## 18. The Road and Transport Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Road and Transport Bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የገጠር መንገዶችን የሚመለከቱ አገር አቀፍ ፖሊሲዎችንና ህጎችን በክልሉ ውስጥ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

2) በክልሉ ውስጥ የገጠር መንገዶች የአዋጭነት ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የገጠር መንገዶችን በተቀናጀ ሁኔታ ያለማል፣ ያሻሽላል፣ እንዲሁም የግንባታም ሆነ የጥገና ስራዎቻቸው ወጪ ቆጣቢና የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፣ የመንገድና የድልድይ ስራዎች በተገባላቸው ውል መሠረት የተከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር ያካሂዳል፤

3) በክልሉ ውስጥ የመንገድ አውታር የሚያድግባቸውንና የሚሻሻልባቸውን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቁለትም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

4) በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው የገጠር መንገዶች ግንባታ ወጥነትና ፍትሐዊ ስርጭት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

5) የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን የሚያወጣቸውን አገር አቀፍ የዲዛይን ደረጃዎች በመከተል ለክልሉ ገጠር መንገዶች የሚያስፈልጉትን ዲዛይኖች በራሱ ወይም በሌሎች ብቁ አማካሪዎች አማካኝነት ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

1) Implement and cause the implementation of nationwise policies and laws concerning to the rural roads, in the region;

2) Carry out and cause the carrying out of feasibility studies of rural roads in the region; develop and maintain the rural roads in integration situation by considering economic feasibility of same, as well as, follow up their construction and maintenance works to be cost effective and standardized; and supervise that the road and bridge works have been performed as their contract agreement;

3) Prepare the short ,medium and long-term plans and programs that the road infrastructure to be developed and improved in the region; submit same to the regional government council and implement upon approval;

4) Approving the rural roads construction to have consistency and fair distribution in the region;

5) Prepare and cause the preparation of using by its own or other qualified consultants, designs for rural roads of the region in line with the standard design issued by Ethiopan Road Authority;

6) የግንባታና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን በራሱ ሀይል ወይም በሌሎች አማካሪዎች አማካኝነት ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ውሎችን ይሰጣል፤

7) ከኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመመካከር የክልሉን ገጠር መንገዶች በሚመለከት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም መሣሪያዎችን ዲዛይን ያዘጋጃል፣ በአስፈላጊው የገጠር መንገድ ላይ ያኖራል ወይም እንዲተከሉ ያደርጋል፤

8) ለጋራ አገልግሎት እንዲውል በየትኛውም አካል ኃላፊነት የሚገነባውና የሚጠገነው ማናቸውም መንገድ ደረጃውን ጠብቆ ሲያገኘው መንገዱን ተረክቦ ያስተዳድራል፤

9) በህብረተሰቡ አማካኝነት የሚገነቡ የማህበረሰብ መንገዶችን በሚመለከት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ተፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍና የስልጠና አገልግሎት ይሠጣል፤

10) የገጠርም ሆነ የማህበረተሰብ መንገዶች አስተማማኝ የመንገድ ጥገና ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው ወይም ብቁ የጥገና ሀይል ኖሯቸው እንዲገነቡ የሚያስችላቸውን መመሪያ ያዘጋጃል፣ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

11) የገጠር መንገዶችን ከጉዳትና አግባብ ካልሆነ የመንገድ አጠቃቀም የተነሣ የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ያስወግዳል፣ እንዲወገዱ ያደርጋል፤

12) በእያንዳንዱ የመንገድ ግንባታና የጥገና ሥራዎች ላይ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ያከናውናል፤

6) Prepare and cause the preparation of the construction and consultancy contracts by its own or other consultants; and render contracts;

7) Design, in consulation with the Ethiopian Roads Authority, traffic control posts and devices relating to rural roads, place and cause to be placed same on rural roads;

8) Posses and administer when it finds up to the standard , the road constructed and maintained by the responsibility of any pertinent body for common service;

9) Coordinate works with regard to roads of the community that shall be constructed by the society; and render the necessary technical support and the training service;

10) Prepare and cause to be implemented directives by which both the rural and community roads are to be carried out based on effective road maintenance plan or maintenance man power; follow up its implementation upon approval;

11) Protect rural roads from damage and to be occured obstructions with regard to abuse same; remove and cause the removal of obstructions from rural road;

12) Perform technically on each road construction and maintenance works at least once a year;

13) የክልሉን የመንገድ ደህንነት ፈንድ ያቋቁማል፣ እንደአስፈላጊነቱ በጥቅም ላይ እንዲውል ያደረጋል፤

14) የተሽከርካሪዎችን ክብደትና መጠን የሚመለከቱ አገር አቀፍ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

15) የሃገሪቱ የትራንስፖርት ዘርፍ የሚመራባቸውን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎችና ፕሮግራሞች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፤

16) የክልሉንም ሆነ የሀገሪቱን የትራንስፖርት አገልግሎቶች ለመምራትና ለመቆጣጠር በክልልና በፌደራሉ መንግስት አካላት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

17) በክልሉ ውስጥ የሚሰጡት የተለያዩ የትራንስፖርት ዓይነቶች ተደጋግፈው የሚያድጉበትንና በተቀነባበረ ሁኔታ በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ስርዓት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

18) የትራንስፖርት መገልገያ ቴክኖሎጅዎችን ያጠናል፣ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ይመዝናል፣ ጥያቄ ሲቀርብለት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

19) የክልላዊ መንግስቱን የትራንስፖርት መገልገያዎች ግዥ ሰነድ ያዘጋጃል፣ ስለ አያያዝና አጠቃቀማቸውም ቴክኒካዊ ድጋፎችን ይሰጣል፤

13) Establish the road safety fund of the region; as deemed as necessary, it may implement same therein;

14) Cause to implement the national laws , regulation and directives with regard to weight and size of the vihicles;

15) Implement, within the region, transport policies, strategies and programs by which the country transport services is guided;

16) Ensure that proclamations, regulations and directives enacted with the region and federal government bodies, to lead and supervise both the region and the federal transport services are observed;

17) design and implement the system of integrated development as well as coordinated utilization of the rendered various transport types in the region;

18) conduct a study for transport service technologies, weight and prepare standard; issue certificate of excellence where requested and thereby cause the proper utilization of same;

19) Prepare the transport facilities procurement document of the regional government; and render technical supports for their handling and utilization of same;

20) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ባለሞተር ተሽከርካሪዎችና ጀልባዎች ይመዘግባል፣ የአሽከርካሪዎችን፣ የካፒቴኖችን፣ የተሽከርካሪዎችንና የጀልባዎችን ብቃት ያረጋግጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንኑ ብቃት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ሌሎች ድርጅቶችን ወይም ተቋማትን በውክልና ያሰራል፣ ይከታተላል፣ ከእነዚሁ አገልግሎቶች የሚገኘውን ክፍያ ይሰበስባል፤

21) ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን ግምት ሥራ ያከናውናል፣ ለስመ ንብረት ዝውውር የሚቀርቡ ባለጉዳዮችን ያስተናግዳል፣ ውል ያዋውላል፣ ዝውውሩ እንዲፈፀም ያደረጋል፤

22) የክልሉን የመንገድ ደህንነት ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፣ በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱትን የመንገድ ደህንነት እንቅስቃሴዎች አቀናጅቶና አስተባብሮ ይመራል፤

23) በከተሞች ውስጥ የpaርኪንግ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አጠቃቀማቸውን የሚያጐለብት ስርዓት ቀርጾ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

24) በክልሉ ውስጥ በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋንና ስምሪት እንዲኖር ያደርጋል፣ የትራንስፖርት ኦፕሬተሮችን ብቃት ያረጋግጣል፣ ፈቃድ ይሰጣል፤

25) የትራንስፖርት አገልግሎቱ በነጻ ስምሪት በገበያ ውድድር የሚመራባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ ለውጤታማ የገበያ ውድድር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እስኪቻል ድረስም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአገልግሎት ታሪፍ፣ ጣራና ወለል ሊወስን ይችላል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

20) Register motor vehicles and boats in the region; ensure the efficiency of drivers, captains, vehicles and boats; where it is necessary, and cause other organizations or institutions perform in delegation that are able to ensure such efficiency; follow up in same and collect service fees from these service;

21) Perform the activity of value estimation of used cars; entertain customers as to the transfer of the title deed of parties; enter into contract, and cause the implementation of transfer service;

22) Protect the safety of roads of the region, and cause the protection of same, integrate and administer coordinately the activities of safety of roads carried out by other bodies in the region;

23) Encourage the expansion of parking services in towns, devise a system to strengthen their use and cause in effect, in collaboration with the pertinent bodies of the issue;

24) Cause the availability of sufficient coverage and trips of transport in the region; ensure the competency of transport operators, and issue license;

25) Facilitate conditions to guide the transport service in market competition, determine. as may be necessary, the ceiling and initial of service tariff until conducive conditions for effective market competition are created; and follow up the implementation of same;

26) በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የትራንስፖርት መገልገያ አምራቾች፣ አስመጭዎች፣ የተሽከርካሪ መጠገኛና ማደሻ ጋራዥች፣ የተሽከርካሪ እንክብካቤ ባለሙያዎች ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች መንዳትን ለሚያስተምሩ ድርጅቶች የሙያዊ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

27) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተሽከርካሪ መናኸሪያዎች፣ ወደቦችና የትራፊክ ኮምፕሌክሶች በግል ፣በመንግስት ወይም በጋራ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ ስታንዳርድ ያወጣል፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ከሚያስተዳድራቸው መናኸሪያዎችና ወደቦች የውስጥ ገቢ ይሰበስባል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

28) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በክልሉ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፍ የሚጠይቁ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ችግሩን ለመቀልበስ ይቻል ዘንድ የመንግስትንም ሆነ የግል ተሽከርካሪዎች ሊያሰማራ ይችላል፤

29) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአካባቢ ብክለትን ይከላከላል፤

30) በክልሉ ውስጥ የትራንስፖርት ማህበራት እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ይመዘግባል፣ ይደግፋል፡፡

## 19.<u>የቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

26) Issue certificate of professional efficiency to producers of transport facilities, importers, vehicle maintenance and repair garages established in the region, to vehicle care giving professionals or organizations who train motor vehicles driving and supervise same thereof;

27) Cause the establishment of vehicle terminals, ports and traffic complexes, in collaboration with the pertinent bodies of the issue, in private, by the government or in common; issue standards of same, direct over and supervise of service rendering, collect internal revenue from vehicle terminals and ports that it administers; and implement properly;

28) Cause the trip of private as well as government vehicles to curve problems occurred under obligatory circumstances and thereto the support of transport service is required in the region, where the particulars shall be determined by regulation, issued for the implementation of this proclamation;

29) Prevent local pollution in collaboration with the pertinent bodies to the issue;

30) Cause to the organization of transport associations in the region, register and support same tehereof.

## 19.<u>**The Technic Vocation and Enterprises Development Bureau**</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Technic Vocation and enterprises Development Bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular power and duties:

1) በክልሉ ውስጥ የቴክኒክና ሙያም ሆነ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅዎች በተገቢው ሁኔታ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣ በስትራቴጅዎቹ አፈጻጸም ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮችን እንዲፈቱ ያደርጋል፣ የስትራቴጅዎቹን አተገባበር ለማፋጠን የተዘጋጁ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብሮችንና እነዚህኑ ለማስፈጸም የተዘጋጁ መመሪያዎችን በስራ ላይ ያውላል፤

2) በገጠርም ሆነ በከተማ አካባቢዎች የሚካሄዱ የስራ ዕድል ፈጠራዎችን ያስተባብራል፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የሚሰማሩ ዜጎችን ይመዘግባል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የስልጠናና የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፣ ኢንተርፕራይዝ ፈጥረው እንዲሰሩ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

3) በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በቂ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች እንዲያገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤

4) የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎችን በማደራጀትና በማጠናከር እንዲሁም የድጋፍ አገልግሎቶችን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችሉ የተሻሻሉና አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከላቱን አቅም ይገነባል፤

5) በክልሉ ውስጥ ከተቋቋሙት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና ከሌሎች በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት የሚረዱ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

1) Ensure the proper implementation of both Technic vocation and micro and small enterprises development strategies through out the region, as well as, cause the solution of the problems that might arise with respect to the implementation of same; implement the prepared support frameworks , the capacity building action plans and directives that have been prepared to execute in same to speed up the implementation of these strategies;

2) Coordinate creating of job opportunity performed both in rural and urban places; register citizens, who work in micro and small scale enterprises; create awareness; cause to be created for them, the training and job opportunity; support them to create and work the enterprise;

3) Work in cooperation with the pertinent bodies of the issue; that to get enough production and selling places of enterprises, which works in this sector;

4) Build up the capacity of one-center service stations by organizing and strengthening them, as well as, putting in place the revised and newer systems enabling to provide such centers with support framework properly;

5) Devise mechanisms that might help to work jointly with the bodies engaged in the sector and thereby facilitate discussion forums;

6) የተለያዩ የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የቴክኒክና ሙያም ሆነ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅን ለህብረተሰቡ በስፋት የማስተዋወቅና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ያከናውናል፤

7) በቴክኒክና ሙያ ረገድ በቂ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ያለው የሰው ኃይል በመገንባት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ወደ ሥራ እንዲገቡ ከአነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ያደርጋል፣ የተጠናከረ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

8) ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎች እንዲመዘገቡ፣ እንዲደራጁ፣ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸውም ሆነ የእድሳት ወይም የስረዛ አገልግሎት እንዲያገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

9) ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ ይደግፋል፣ የገበያ ትስስሮችን በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያግዛል፤

10) በክልሉ ውስጥ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የእሴት ሰንሰለት ጥናቶችን በማካሄድ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ የትምህርትና ሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጅና የምክር አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያደርጋል፤

6) Undertake the activities of awareness-creation, and widely familiarizing both the technic vocation and micro and small scale enterprises development strategy to the community by using the various mass-media systems;

7) Facilitate the condition in which the micro and small scale enterprises might be able to obtain an industrial extension service and access to credit with a view to enabling them get into operation, in collaboration with the technical and vocational education and training, as well as, the small-scale financing institutions;

8) Render the necessary support to the micro and small scale enterprises to be registered, organized, and secure a certified of legal personality along with the renewal and cancellation services through the one – center service stations;

9) Support the micro and small scale enterprises so that they would be organized in association in accordance with their respective fields as well as cause same to benefit from the marketing network thereof;

10) Cause the provisions of training, financial, technological and consultancy services based on the interests of micro and small-scale enterprises by having conducted value chain studies with regard to the manu facturing sector in the region;

11) የሞዴል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርጥ ተሞክሮዎች ያጠናል፣ ይቀምራል፣ ያስፋፋል፤

12) በክልሉ ውስጥ ወጥ የሆነ የመረጃ ሥርዓት እንዲደራጅ በማድረግ ለዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

13) በቴክኒክና ሙያ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅ መሠረት ኢንተርፕራይዞችን ይደግፋል፣ የደረጃ ደረጃ ሽግግር የሚያደርጉ ኢንተርፕራይዞችን ይለያል፣ የዕውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

14) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የሂሣብ አያያዝና የኦዲት አገልግሎት በራሱም ሆነ በልዩ ልዩ አማራጮች እንዲያገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

15) በክልሉ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ የመንግስትና የግል ፖሊ ቴክኒክና የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጆች እንዲሁም የአጫጭር ስልጠና መስጫ ተቋማት ዕውቅና ይሠጣል፣ ከደረጃ በታች ሆነው ሲገኙ ዕውቅናቸውን ያነሳል፤

16) አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚመለከት ሥርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅና በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

17) በዘርፉ የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የሚያስችሉ የምርምርና የቴክኖሎጅ ልማት እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

11) Study, organize and replicate the best practices of model technic vocation colleges, as well as the micro and small-scale enterprises;

12) Collect, analyse, and organize information necessary for the development of the sector by causing the organization of a unifrm information system in the region, as well as, distribute same to the beneficiaries;

13) identify those enterprises capable of being transformed from the stage of small –scale ones to that of developing and medium-level institutions based on the development strategy of the micro and small –scale enterprises and render the certificate of recognition;

14) render the necessary support, for the micro and small scale enterprises' book account maintaining and audit service by itself, as well as ,by various alternatives;

15) render license for the government and the private polley technic and the training colleges of the technic vacation; as well as , institutions that used for rendering short term trainings; cancel their license where they shall be found below the standard;

16) cause the curriculum to be prepared and shall be in effect, that is concerned to short-term trainings;

17) coordinate and support the research and technology development activities to be developed, that enable to speed up the region's social and economical development by the pertinen sector;

18) ተጠሪዎቹ ለሆኑለት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ውጤታማ የሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት ይቻላቸው ዘንድ ተቀባይነት ያለው የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም የፋይናንስ ሥርዓት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

19) የግል ባለሀብቶች፣ ህብረተሰቡ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በኢንተርፕራይዞች ልማትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን ሥልት ይቀይሳል፤

20) የቴክኒዎሎጅ ምርምር፣ የፍተሻ ቤተ-ሙከራ፣ የኢንዱስትሪ አሠራሮችና ተሞክሮዎች ማስተዋወቂያና የምክር አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን የማስተዋወቅ የተለያዩ የፍተሻ /የኬሚካል ትንተና፣ የመካኒካል ሙከራ፣ የብረታ-ብረት፣ የልኬታና እነዚህን የመሳሰሉትን የምክር አገልግሎቶች ይሠጣል፤

21) የቴክኒዎሎጅ ሽግግር ለሚያካሂዱ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ይሠጣል፣ የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፤

22) በቴክኖሎጅ ጥናትና ምርምር ረገድ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሠራል፤

18) Make a suitable condition of establishing finance system, that enables to render effective technic vocation education and training colleges of the technic-vocation, those are accountable to the Bureau, and follow up its implementation;

19) Devise a strategy for those,who participate in sector of enterprises development and the technic-vocation education and training, of the private investors, the society , micro and small-scale enterprise, governmental and non-governmental organizations;

20) Establishing technological research, laboratory, industrial procedures and practices informing and rendering the counseling service centers; informing new technology for micro and small –scale enterprises; rendering different tests such as /chemical analysis , mechanical test, general mechanics or manufacturing , measurement and similar counseling services;

21) Render the finance and the technic support service for the micro and small-scale enterprises, that conduct a technology transfer, and shall set system of incentives;

22) Perform in collaboration and integration, together with higher educational institutions and other similar bodies, with regard to technology and research work in the region;

23) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የርስ በርስ መደጋገፍና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያስተዋውቁ ኤግዚቢሽኖችን፣ ባዛሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፤

24) የክልሉ ቴክኒክና ሙያ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 20.<u>የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርna አጠቃቀም ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የገጠር መሬት አይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፣ አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2) መሬቱ በተለያዩ ምክንያቶች ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጪ እንዳይሆን የመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎች ማድረጋቸውን ይከታተላል፣ መሬታቸውን በአግባቡ ለያዙት የተለያዩ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ግዴታቸውን በማይወጡት ላይ ደግሞ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

3) እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሳ ዘዴዎችን በመጠቀም እያንዳንዱን የመሬት ይዞታና ማሳ ይመዘግባል፣ በምዝገባው መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል፤

23) Prepare exhibitions, bazars, and festivals that shall introduce supporting to each other and world competitiveness of the micro and small –scale enterprises;

24) Facilitate the establishment of the technic vocation and the mocro and small-scale enterprises of the region development council and coordinate its activities thereof;

## 20. <u>The Rural Land Administration and Use Bureau</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the regional bureau of rural land administration and use shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1 ) study, register and maintain the type and amount of rural land available in the regional state, follow up and supervise over its management and utilization thereof;

2) follow up that land users take care of their land holdings in various ways, so that the land may not lose its productivity and become useless due to a variety of factors; devise various incentive methods for those who hold their land properly; and take measures on land holders who don’t discharge their own duties;

3) having regard to circumstances, using traditional and modern surveying instruments, register each and every land-holding and plot and thereby issue a certificate of holding with a map as per such registration;

4) የመሬት ይዞታ መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የይዞታ መብታቸውን እንደአግባብነቱ በውርስ፣ በኪራይ፣ በስጦታ ወይም በለውጥ የሚያስተላልፉበትን ስርዓት ያስፈጽማል፣ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን በየጊዜው እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደረጋል፤

5) የግል ባለሀብቶች በመሬት ላይ የልማት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የአጠቃቀም እቅዳቸውን እየገመገመ ያፀድቃል፣ የኢንቨስትመንት መሬት ሊዝ አሰራርና ተመኑን በየጊዜው እያጠና ለክልሉ መንግሥት በmeብ ያስወስናል፣ ከባለሀብቶች ጋር ውሎችን ይፈጽማል፣ በዕቅዳቸውና በውላቸው መሠረት ተግባራዊ በማያደርጉት ላይ ደግሞ በህግ አግባብ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወስዱ ያደርጋል፤

6) ለገጠር ቀበሌ ማዕከላትና አዳዲስ ለሚፈጠሩ አነስተኛ ከተሞች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማዘጋጀት ይረዳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

7) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግስትና የከተማ አስተዳደር አካላት ጋር በመተባበር ለህዝብ ጥቅም ታልሞ በሚወሰድ እርምጃ ምክንያት ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ባለይዞታዎች ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ እንዲከፈላቸውና አማራጭ የኑሮ መሠረት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

8) በዘመናዊ ሁኔታ በሚለሙ ትላልቅ የመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚኖሩ ቀደምት ባለይዞታዎች በህግ አግባብ የመሬት ሽግሽግ በማካሄድ የሁለተኛ ደረጃ ደብተርና ካርታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

4) Cause the execution of the system through which individuals or organizations having been conferred with the land –holding rights may, as appropriate, be able to transfer such rights by inheritance, lease, bequeath or exchange, as well as, register any alterations that might be occasioned on the land from time to time, and henceforth update the data in its possession;

5) Evaluate and approve the land utilization plan of those private investors prior to the commencement of their development activities, study, from time to time the investment land lease procedure and rate and have it determined by the regional government, conclude contrcats with the properietors and cause the taking of actions, pursuant to law against those failing to perfrom in accordance with their plans and contracts;

6) Assist in the preparation of land use plans for the rural kebele centers and newly-emerging and small urban settlements, as well as, follow up their implementation;

7) In collaboration with the regional government and urban administration bodies of the issue, cause in favor of those land holders uprooted from their lands due to measures to be taken in view of public interests, so that the latter shall be paid equitable compensation in advance and have alternative basis of livelihood;

8) Having carried out land redistribution in accordance with law, cause the acquisition of second-grade holding certificate along with a map for those original inhabitants inside the large scale irrigation protect areas being developd in a modern ways;

9) በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ አስተዳደራዊ እርከኖች፣ ይዞታዎችና ማሳዎች ልዩ ኮድ ይሰጣል፣ የተሰጠውን መለያ ኮድ ሌሎች መ/ቤቶችና የልማት ተቋማት እንዲገለገሉበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

10) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የተጠቃለሉ የገጠር ቀበሌዎችን መሬት-ነክ አስተዳደርና አጠቃቀም ይወስናል፣ ይመዘግባል፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል፡፡

## 21. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉ መንግስት አካላት በወጡት የፋይናንስ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤

2) በክልሉ መንግስት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን መደበኛና የካፒታል በጀት ሐሣቦች መርምሮ የክልሉን አጠቃላይ ዓመታዊ በጀት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ የተዘጋጀውን የበጀት ረቂቅ ከአስተያየት ጋር ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፣ የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል፤

3) የክልሉን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለፌደራሉ መንግሥት ያሳውቃል፣ ፋይናንስ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከፌደራሉና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል፤

9) Render a special codes to the administrative hierarchies, land holdings and plots available in the regional state and thereby facilitate conditions whereby offices and developmental institutions might use such identification codes;

10) Decide on the land –related administration and use matters involving rural kebeles incorporated into the jurisdiction of urban administrations, as well as, register same and thereby issue land holding certificate and maps, in collaboration with the appropriate bodies;

## 21. The Finance and Economy Collaboration Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisiobns to other laws, the finance and economy collaboration bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Supervise over the operation of the regional government bodies in compliance with the financial policies, laws, regulations and directives in force;

2) Having examined the recurrent and capital budget proposals prepared and submitted to it by the regional government bodies, gather data enabling it to prepare the consolidated annual budget of the regional state in an equitable manner, and submit the draft budget to the regional state along with its recommendations and administer same upon approval;

3) Prepare periodic statements of a comprehensive nature indicating the fiscal undertaking and financial position of the regional state and submit same to the council of the regional government, notify same to the federal government, as deemed as necessary, and work in harmony with the federal and other relevant institutions with regard to financial matters;

4) የክልል መንግሥቱን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይመሠርታል፣ ይኸው በክልሉ መንግስት አካላት አማካኝነት በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

5) የክልሉን ዓመታዊ የገቢና የወጭ ሂሣብ በወቅቱ ያዘጋጃል፣ ለኦዲት ተግባር ምቹ ያደርጋል፤

6) ከአገር ውስጥና ከውጭ የሚገኙ ዕርዳታዎችን፣ ብድሮችንና ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የሚደረጉ ስምምነቶችን በክልሉ መንግስት ስም ይፈራረማል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

7) ከሌሎች የፌደራሉ መንግስት አካላትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝን ሀብትና ንብረት በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ከሚመለከታቸው የሴክተር መስሪያ ቤቶች ሪፖርቶችን ይቀበላል፤

8) የክልል መንግስቱን የዕቃና የአገልግሎት ግዥና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

9) በክልሉ መንግሥት አካል ሥር ለማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ላልዋለ የክልሉ መንግሥት ሀብትና ንብረት ኃላፊ በመሆን ይሠራል፣ ያስተዳድራል፤

10) የክልሉ ሀብትና ንብረት ውጤታማ በሆነ መንገድ በሥራ ላይ እንዲውል ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ በባለበጀት መስሪያ ቤቶች ዘንድ አቅም እንዲፈጠር ያደርጋል፣ የውስጥ ኦዲት አሠራሮቻቸውን ያጠናክራል፤

11) የክልሉን የገቢ አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎችንና የአሰራር መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።

4) Establish the accounting system of the regional state and supervise over its implementation on the part of the regional government bodies ;

5) Prepare timely the annual revenue and expenditure accounts of the regional state and thereby facilitate same for audit purposes;

6) Sign on behalf of the regional state agreements concluded with regard to internal and external assistance, loans and projects, monitor and evaluate their implementation thereto;

7) Follow up closely and oversee the resources and property that may be generated from other federal government bodies and non-governmental organizations and thereby receive reports from the pertinent sectoral offices;

8) Prepare the regional goods and services' procurement and use directives and supervise over its implementation thereof;

9) Be in charge of and administer the resources and property belonging to the regional state, which is not otherwise managed by any regional government body or not destined for use;

10) Put the appropriate working procedure in place to utilize the regional resources and property in an expedient manner , cause the creation of capacity on the part of the budgetary offices and thereby strengthen their internal auditing operation;

11) Prepare the policy frameworks and working procedures enabling to enhance the revenue – raising capacity of the regional state and thereby follow up their implementation.

## 22. <u>የትምህርት ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂያዊ እቅዶችና ፕሮግራሞች አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

2) አገራዊ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት ክልል አቀፍ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በስታንዳርዱ መሠረት መሟላቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

3) አገራዊ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ተግባራዊ የጐልማሶች መሠረታዊ ትምህርት፣ የአፀደ ህፃናት፣ የልዩ ፍላጎት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲሁም የመምህራን ትምህርት ሥርዓተ ትምህርቶችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ያሻሽላል፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማቴሪያሎች በነፃው ገበያ በማወዳደር በጥራት እንዲታተሙና እንዲሠራጩ ያደርጋል፣ መፅሀፍቱም በገበያ ላይ መገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

4) የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅን ተግባራዊ በማድረግ ለክልሉ ብሎም ለአገሪቱ አጠቃላይ ልማት እውን መሆን ምክንያት የሚሆን ብቁ ዜጋ የሚፈራበትን ስልት ይቀይሣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ሂደቱንም በየጊዜው እየገመገመ ያሻሽላል፤



## 22. <u>The Education Bureau</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws , the education bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Prepare and implement the short, medium and long –term strategic plans and programs of the regional state on the basis of the country's eduction and training policy, follow up and evaluate same and provide support necessary thereof;

2) Set standards for the educational institutions at all levels in line with country-wise standards; follow up and oversee their compliance thereof, as well as, take corrective measures, as may be necessary;

3) prepare, in line with the national standards, the curricula of practical and basic adult education, kindergarten, special needs' education, primary and teachers' education, follow up their implementation thereof, evaluate and revise same, cause the publication and distribution of the curriculum materials in the competitive free market with the desired quality and thereby ensure the availability of the books for sale;

4) Having implemented the comprehensive education quality assurance package devise a mechanism through which a competent citizenry, able to realize the overall regional development, might be cultivated; implement and follow up same and revise its process through periodic evaluations;

5) የትምህርት አቅርቦቱን ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማስፋፋት የሚረዱ ልዩ ልዩ ስልቶችንና አማራጮችን በመንደፍ ጥራት ያለው መሠረታዊ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፤

6) በክልሉ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታና ፍላጎት ያገናዘበ፣ የጾታ፣ የቦታና ማህበራዊ ሚዛናዊነትን የጠበቀ፣ ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያግዝ ሆኖ ዴሞክራሲያዊና ሣይንሳዊ አስተሣሠቦችንና አሰራሮችን ለማጎልበት የሚረዳ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7) በክልሉ ውስጥ ከቅድመ መደበኛ ትምህርት አንስቶ እስከ ከፍተኛ ትምህርት የሚደርሱ ተቋማትን ያደራጃል፣ አዳዲሶችንም ይከፍታል፣ አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ግብአቶችን ለማሟላት የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

8) የተለያዩ የትምህርት ፕሮግሞች በትምህርት መገናኛ ዘዴዎች እንዲደገፉ በማድረግ ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለህብረተሰቡ ትምህርት ይሰጣል፤

9) የመምህራንን፣የርዕሳነ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ብቃት ለማሳደግ የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱ ውጤት መሠረትም የቅድመ ሥራ ሥልጠና እንዲሁም ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ሂደቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

10) ለትምህናት ተቋማት የእውቅና ፈቃድ ይሠጣል፣ ያድሳል፣ እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ መምህራን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፤

5) See to it that all are provided with access to quality and basic education by formulating various mechanisms and alternatives assisting to promote the educational provisions in a balanced and equitable manner;

6) Follow up and monitor that the education being provided throughout the regional state is of such a nature that reflects the objective realities and needs of the locality, preserves gender, spatial and social balance, assists in practical actions and is such instrumental to strengthen the democratic ideals and deeds;

7) Organize educational insttutions starting from pre-regular education up to higher education, open new ones in the region; devise various mechanisms with the view to fulfill the necessary educational inputs and follow up their implementation;

8) Provide education for students, teachers and the community by having various educational programs supported through the education media system;

9) With the view to enhancing the competence of teachers, directors and supervisors conduct needs assessment studies, cause the delivery of pre-service, as well as, continuing professional improvement trainings as per the result of such study, follow up the process, evaluate same and take corrective measures thereof;

10) Issue and renew license of recognition for educational institutions, as well as, award and renew certificate of competence for teachers at all levels;

11) በትምህርት ተቋማት የሚካሄደውን የትምህርት አሠጣጥ አስመልክቶ የትምህርት ጥራት ኦዲት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወሠዱ ያደርጋል፤

12) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ ውጤቱንም ይወስናል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎችን በክልሉ ውስጥ ያስፈፅማል፤

13) በተመረጡ የክፍል ደረጃዎችና ተማሪዎች ላይ ክልላዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱም መሠረት የመፍትሔ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

14) ልዩ ልዩ የትምህርት ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላትና ለሌሎች ድርጅቶች ያሰራጫል፣ ለመረጃ ስብሰባና ትንተና የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርአት ይዘረጋል፤

15) በየአካባቢው የሚገኘው ህብረተሰብ በየጊዜው በትምህርት አመራሩ፣ በበጀት አመዳደቡና አፈፃፀሙ ላይ ሙሉ ተሣትፎና ቁጥጥር ኖሮት ትምህርት ቤቶችን በባለቤትነት የሚመራበትን፣ የሚደግፍበትንና የሚቆጣጠርበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

16) በክልሉ ውስጥ ትምህርትን ከማስፋፋትና ጥራቱን ከመጠበቅ አንፃር ልዩ ልዩ ሥልቶችን በመንደፍ በህብረተሰቡ፣ በግለሰቦችና በድርጅቶች አማካኝነት ተጨማሪ የትምህርት ሀብት ያፈላልጋል፣ ይህንኑ ለትምህርቱ ሥራ ያውላል፤

11) Carry out educational quality audit with regard to the educational institutions, take corrective measures and cause same to be taken thereof;

12) Prepare and deliver first cycle education leaving examinations and determine the results, as well as, executed in the regional state, those examinations prepared at the national level;

13) Undertake regional education enrollement studies on selected grades and students and thereby take rectifying measures as per the results of such study;

14) Collect, analyse and compile various statistical data concerning to education, transmit same for the pertinent bodies and other organizations and put in place modern information system, instrumental for data collection and analysis;

15) Install and materialize a system in which the community living in each and every neighborhood might, having had full participation in and control over the management of education along with its budgetary allocation and execution therewith, be able to direct, support and monitor schools with ownership thereof;

16) Seek for additional resource and employ same for educational purposes via the agency of the community, private persons and organizations, by having formulated various mechanisms from the standpoint of promoting education and preserving its quality throughout the regional state;

17) ለትምህርት የሚመደበውን በጀትና ንብረት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ አጠቃቀሙም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን ያረጋግጣል፤

18) በሥራ ላይ ያሉና ትምህርት ነክ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከወጡበት አላማና ተግባር አንፃር በሥራ መተርጐማቸውን ያረጋግጣል፤

19) የትምህርት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ውሣኔዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ እቅዶችን አፈፃፀሞችንና የመሳሰሉትን መረጃዎች በተለያዩ የህዝብ ግንኙነት አግባቦች በመጠቀም ለህብረተሰቡና ለትምህርት ያገባኛል ባዩች የማድረስ ሥራ ያካሂዳል፡፡

## 23.<u>የጤና ጥበቃ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ስትራቴጅ መሠረት በማድረግ የክልሉ ህዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

2) ስለ ህዝብ ጤና አጠባበቅ የወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

3) በየደረጃው የሚገኙትን የጤና ተቋማት፣ የጥናትና ምርምር ማዕከላትና የማሰልጠኛ ተቋማት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤

4) በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፤

17) Organize and administer the budget and property set aside for education as well as ensure that its utilization is cost effective and expedient thereto;

18) Ascertain that the education-centered policies, laws, regulations and directives in effect are interpreted into practice, in the light of the purposes and duties of their issuance;

19) Undertake the activities of communicating to the community and stake holders using the various public relation channels, information on educational policies, programs, decisions, services, plans, implementation and the like;

## 23. <u>The Health Bureau</u>

Without prejudice to existing or subsequent provisions of other laws, the regional bureau of health shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1. Prepare in line with the country's health policy and strategy, the health care plans and programs whereby the health of the community in the regional state might be protected and implement same upon approval, as well as, cause the expansion of health services therein;
2. Ensure the due observance of laws, regulations and directives issued on public health, throughout the regional state;
3. Organize and administer the health facilities, study and research centers and training institutions found at all levels;
4. Supervise that the drug supplies and medical equipment destined for use in the regional state are in conformity with the required quality and standards;

5) በክልሉ ውስጥ በግል ባለሀብቶችና በድርጅቶች ለሚቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ የዲያግኖስቲክ ማዕከላትና መድኃኒት ቤቶች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጡትን መስፈርቶች ጠብቀው መስራታቸውን ይቆጣጠራል፤

6) አዲስ የሚቋቋሙ የመንግሥት የጤና ተቋማት አስፈላጊውን ደረጃ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ሥራ እንዲጀምሩ ያደርጋል፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7) በክልሉ ውስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ለዚሁ የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

8) ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድኃነቶችና የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ ህክምና ጋር ተዋህደው በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ባለሙያዎችን ያደራጃል፣ ለዘርፉ የወጣውን ህግና ደንብ ጠብቀው መሥራታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤

9) የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ ለማስፈፀም የተዘረጉና የሚዘረጉ ፕሮግራሞችንና ስትራቴጅዎችን በክልሉ ውስጥ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

10) የጤና መሠረተ ልማት ግንባታዎችን ያስፋፋል፣ አስፈላጊ ግብዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

11) የህዝብ ጤና እንዲጠበቅ ለማድረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ያካሂዳል፤



5. Issue professional license with regard to health stations, clinics, diagnostic centers and drug stores or shops that might be established by private investors and organizations in the regional state and oversee that they carry out their operations in compliance with the national standards;

6. Cause the newly-established public health facilities to commence official duties, after having ascertained that they comply with the required standards, as well as, follow up and monitor their service delivery thereof;

7. Ensure and supervise that the professionals engaged in the public health service activities throughout the regional state have met with the standards set for such duties;

8. Cause the application of traditional medicines and treatment methods, whose curative nature has been ascertained, in integration with contemporary medications, organize professional of same and supervise over their activities, as to whether they are in compliance with the laws and regulations issued for the sector;

9. Execute the programs and strategies set out or to be set out to implement the national health policy and have same executed throughout the regional state;

10. Expand the health infrastructure constructions and ensure that the necessary inputs are fulfilled therewith ;

11. Undertake quarantine controls with the view to taking care of public health;

12) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የመንግሥትም ሆነ የግል የጤና ኮሌጆች ለሚመረቁ የጤና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈተናና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሙያ ምዝገባ ያደርጋል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፤

13) በመከላከል ላይ አተኩረው የሚፈፀሙ የጤና ልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈጽማል፤

14) በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የጤና-ነክ ምርምር ስራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈጽማል፤

15) ለጤናው ዘርፍ ዕድገት የገንዘብ ማግኛ ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙንም በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

16) በክልሉ ውስጥ የጤና መድህን ስርዓትን ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

17) የሀይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

18) የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችንና የወረርሽኞችን ክስተት ይተነብያል፣ ይቃኛል፣ የዳሰሳ ጥናቶችና ዝግጅቶችን ያካሂዳል፣ እንዳስፈላጊነቱ ፈጣን ምላሽ ይሠጣል፣ የመልሶ ማቋቋም ተግባራትን ያከናውናል፤

19) በጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት፣ ለእናቶችና ህፃናት ጤና አጠባበቅ፣ እንዲሁም ኤች.አይ ቪ/ ኤድስን፣ ወባንና የሣንባ ነቀርሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

20) የክልሉን የጤና መረጃ ስርዓት ይዘረጋል፣ በጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

12. In collaboration with the pertinent bodies of the issue, administer competence assurance examinations and certificates for those health professionals, who shall have graduated from the public and private health colleges residing in the regional state, effect professional registration, issue and renew license thereof;

13. Coordinate, direct and cause to execute health development activities implemented focusing on prevention;

14. Coordinate, direct and cause to execute the health related research works undertaken in the regional state;

15. Put a health care financing system in place for the promotion of the sector, as well as , direct and supervise over its implementation thereof;

16. Put in place the health insurance system in the region; implement same and follow up its implementation;

17. Direct and supervise over the hygiene and environmental health care activities;

18. Forecast, it might necessary the possible occurrence of public health emergency and epidemic phenomenon, undertake survillance, exploratory studies and preparatory works, provide with a rapid response and conduct rehabilitation activities thereof;

19. Strive towards the achievement of the sustainable development goals, as regard to the health care sector rendering with a special emphasis on the health care for mothers and children, as well as, the prevention and control of HIV/AIDS, malaria and TB diseases;

20. Put in place the regional health information system and cause its utilization thereof;

21) በክልሉ ውስጥ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የህዝብ ጤና አጠባበቅ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ጥፋተኞች ሆነው ሲገኙም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

22) የግል ክሊኒኮች፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ተቋማት፣ ሆስፒታሎችና የመድኃኒት ንግድ መደብሮች፣ የመንግስትን ደንብና መመሪያ ተከትለው መሥራታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ጥፋተኞች ሆነው ሲገኙም እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

23) በአዳዲስ የጤና ተቋማት ዘንድ ልዩ ልዩ የጤና አገልግሎቶች እንዲጀመሩ ጥያቄ ሲቀርብለት ይፈቅዳል፣ ደረጃቸውን ጠብቀው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

24) የሃገሪቱ የኤች አይ ቪ ኤድስ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በተቀናጀ መንገድ ይተገበር ዘንድ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

25) በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ተገቢውን ሥልጠናና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በየደረጃው የሚገኙ አካላት ለችግሩ ይበልጥ ልዩ ትኩረት ሰጥተው የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማጎልበት ይቻል ዘንድ የተሟላ ድጋፍ በማሰባሰብ እንዲንቀሣቀሡ ያበረታታል፤

26) በክልሉ ውስጥ ለኤድስ በሽታ የማያጋልጥ የተሟላ ግንዛቤ እና ጤናማ ባህሪ ይጐለብት ዘንድ የክልሉን ህብረተሰብ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ይቀሰቅሳል፤

21. Follow up closely and supervise that the food and drink service delivering establishment in the regional state operate in compliance with the public health regulations and directives in force and take administrative measures against those found to be at fault or cause same to be taken thereof;

22. Supervise over the private clinics; laboratory examination institutions, hospitals and drug dealers and operate in compliance with the government regulations and directives and take administrative measures against those found to be at fault or cause same to be taken thereof;

23. Authorize, upon request the commencement of various health services on the part of those newly established health institutions, as well as, follow up and supervise over their activities as per the standard;

24. Render an overall support for the country's HIV/AIDS policy that shall be implemented in integration within the region;

25. Facilitate condition that the organizations and individuals, that work on the HIV/AIDS prevention and control activities, to get the appropriate training and support; encourage bodies at different levels to work in same by collecting a fulfilled support to be able to promote the society's awareness by giving special emphasis more for the problem;

26. Aware the society of the region using different methods that fulfilled awareness and healthy conduct not to expose for AIDS to be strengthened in the region;

27) ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች ለበሽታው በይበልጥ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ራሣቸውን ከበሽታው ለመከላከል ይቻላቸው ዘንድ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

28) ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች፣ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ ታዳጊ ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው ሰብአዊ መብታቸው የተከበረ እንዲሆን ያደርጋል፣ ይኸው በሌሎች ዘንድ መጠበቁንም ያረጋግጣል፡፡

## 24. ፍትህ ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ፍትህ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉ ፍትህ ሥርዓት የሚሻሻልባቸውንና የሚጐለብትባቸውን የጥናትና ምርምር ስራዎች ያካሂዳል፤
2) የህግ ጉዳዩችን በሚመለከት የክልሉን መንግሥትና ተቋማቱን ያማክራል፤
3) የክልሉ ህብረተሰብ መብትና ግዴታውን አውቆ ህግ አክባሪና አስከባሪ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴዎች የንቃተ-ህግ ትምህርት ይሰጣል፤
4) ሙያዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አካላት ጥያቄ ሲያቀርቡለት በክልሉ መንግሥት የሚወጡ ህጐችና ደንቦችን ያረቃል፤
5) የክልሉን መንግሥት ህጐች በተመለከተ የኮዲፊኬሽንና የማጠቃለል ሥራዎችን ያከናውናል፤
6) የየደረጃውን ዓቃቢያነ-ህግ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

27. Cause to get the necessary information of women, youths and other parts of the society, who are highly exposed for this disease, to be able to prevent themselves from same;

28) cause to be respected the rights of people who live with the virus, patients and orphans due case AIDS, youths and their families; and ensure same to be respected by others.

## 24. The Justice Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the justice bureau shall, pursuant to this proclamation; have the following particular powers' and duties:

1) Conduct study and undertake research as to the ways in which the regional justice system shall be improved and strengthened;
2) Advise the regional government and its institutions with regard to legal matters;
3) Render legal awareness education, using various means, to the community of the regional state so that the latter become law-abiding and enforcing in cognizance of its rights and duties;
4) When bodies request to get professional support necessary, draft such laws and regulations as are to be issued by the regional government;
5) Carry out the activities of codifying and consolidating with regard to laws of the regional state;
6) Direct and supervise over the prosecutors at all levels;

7) በህግ መሠረት በድርድርና በእርቅ እልባት ማግኘት የሚችሉ የወንጀል ጉዳዮችን አይቶ ይወስናል፤

8) የእጅ ተፍንጅ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ውሣኔ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ለዚህም ከፖሊስና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

9) በማረሚያ ቤት፣ በማረፊያ ቤት፣ በጠባይ ማረሚያና በጊዜያዊ የእስረኞች መጠለያ ስፍራዎች የሚገኙ ሰዎች በአግባቡ መያዛቸውንና ህጋዊ መብታቸው መከበሩን ያረጋግጣል፤

10) በክልሉ መንግሥት ፍ/ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖረው የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን መመሪያ ይሰጣል፣ በህግ መሠረት የወንጀል ክስ ይመሠርታል፣ ያነሳል፤

11) ለወንጀል ጉዳይ ምስክሮች በወቅቱ መጥሪያ እንዲያደርስና ምስክሮችንም ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ለፖሊስ ትእዛዝ ይሰጣል፤

12) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

7) Consider and decide on criminal cases which are in the nature of being settled through negotiation and concillation pursuant to law;

8) Facilitate the ways in which flagrant offences might be decided in an accelerated procedure where same is found being executed; and to this end, work in collaboration with the police and other bodies pertaining thereto;

9) Ensure that those persons confined prisons, police cells, disciplinary centers and temporary detention facilities are properly handled and their rights are respected;

10) Where it is of the opinion that an offence has been committed, falling under the jurisdiction of the regional courts, order the carrying out of an investigation, issue instruction, on sufficient grounds, for the termination of an ongoing investigation or the conduct of further investigation, as well as, initiate criminal charges or withdraw same, in accordance with law;

11) Instruct the police so that it may serve summons on to the witnesses of criminal cases on time and produce same to the courts;

12) Accord the appropriate protection to the prosecution witnesses, as deemed as necessary;

13) በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት የደረሰባቸውንና ገንዘብ ከፍለው መከራከር የማይችሉ ወይም አቅም የሌላቸው ሰለባዎች፣ የአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ድሀ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት ወይም የኤች.አይ ቪ/ኤድስ ህሙማንን ወክሎ በድርድር ወይም በክልሉ ፍ/ቤቶችና በሌሎች የዳኝነት አካላት ዘንድ ክስ በመመስረትና በመከራከር እነዚሁ ወገኖች ካሣ እንዲያገኙና ፍትሐብሔር ነክ ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩ ያደርጋል፤

14) የክልሉን መንግሥትና ህዝብ መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ይቻል ዘንድ በልዩ የሥራ ጠባያቸው ምክንያት የራሣቸው ነገረፈጅ ካላቸው መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውጭ ያሉትን ክልላዊ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በመወከል በፌደራልና በክልል ፍ/ቤቶች፣ በማናቸውም የዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባኤ ክስ ይመሠርታል፣ ይከራከራል፤

15) በልዩ ሁኔታ የራሣቸው ነገረፈጅ ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ተከራካሪ በሚሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክሶችና የመብት ጥያቄዎች ላይ የህግ ድጋፍ ሲጠይቁ እገዛ ያደርጋል፤

16) በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚነሱ ፍትሐብሔር ነክ የመብት ጥያቄዎችን በማደራደር የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

17) በህግ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የህብረት ሥራ ማህበራትን በመወከል ክስ ይመሠርታል፣ይከራከራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የህግ ድጋፎችን ይሰጣል፤



13) Having represented those victims with a heavy bodily injury as the result of criminal act unable to carry out litigations with pay or lack capacity thereof , poor women vulnerable to risks, persons with disabilities, the elderly, children of HIV/AIDs patients, cause such parties obtain compensation and have their civil interests respected either through negotiation or instituting actions and conducting peleadings in the regional courts and other judicial organs,

14) In view of ascertaining the protection of the rights and interests of the regional state and the people at large, represent the regional government offices and public enterprises, with the exception of those having their own attorneys because of the special characteristic of their duties, institute civil proceedings and carry out pleadings in the federal and regional courts, any judicial tribunal of assembly of elders;

15) Provide assistance, upon request for legal support to those regional government offices and public enterprises having their own attorneys in a special way, with respect to civil claims and proceedings in which they are involved as parties thereto;

16) Cause the amicable settlement of civil disputes involving two or more regional government offices through a negotiated deal;

17) Institute civil actions and plead on behalf of cooperative societies beyond and above the financial limit to be determined by law, as well as, render other types of legal support , as may be necessary;

18) ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ድሀ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍትህ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ የጠበቆችን ማህበራት ወይም ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ያላቸውን የሲቪል ማህበራት በማስተባበር ነፃ የህግ ድጋፍ የሚያኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

19) በክልሉ መንግሥት ፍ/ቤቶች መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች የስራ ፈቃድ ይሰጣል፣ያድሣል፣ ይቆጣጠራል፣ይሰርዛል፤

20) በክልሉ ውስጥ የሰነዶችን ህጋዊነት ያረጋግጣል፣ ይመዘግባል፡፡

## 25. <u>የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ ህግና ስርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሠላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

2) ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለማፍረስና በስውር የህዝቡንና የመንግስትን ጥቅም ጉዳት ላይ ለመጣል የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ድርጅቶችን በመከታተል ተግባራቸውን ያመክናል፣ ጥበቃ ያደርጋል፤

3) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በትርፍ ላይ ያልተመሠረተ ዓላማ ይዘው የተቋቋሙና በክልሉ ውስጥ የሚንቀሣቀሱ ማህበራትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የሀይማኖት ተቋማትን ህጋዊነት በማረጋገጥ ይመዘግባል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤

18) By having coordinated the advocate associations and civil societies with a special professional license thereof, facilitate conditions whereby the poor and vulnerable sections of the community are provided with legal aid free of charge;

19) Issue and renew license, supervise and delete same in respect of advocates capable of pleading before the courts of the regional state;

20) Ascertain the legality of and regioter documents and association in the regional state;

## 25. <u>The Administration and Securtiy Affairs Bureau</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws , the administration and security affairs bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Follow up and ensure the maintenance of law and order in the regional state and the protection of peace and security of the community thereof;

2) Pursue the activities of those individuals , groups and prganizations bent on dismantling the constitutional order by force and thereby jeoparadize public and government interests in aclndestine manner, paralyze such activities and provide protection thereof;

3) In collaboration with the appropriate bodies , having ascertained their legality, regioter associations established with a non –profit objective and hence forth operate in the regional state, non governmental organizations and regious institutions, supervise and cancel same in collaboration with the pertinent bodies;

4) በክልሉ ውስጥ በሚገኙት የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ነዋሪ ህዝቦች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

5) በክልሉና በአጐራባች ክልሎች መካከል የሚነሱ ግጭቶችና አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ሊፈቱ የሚችሉባቸውን ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፤

6) የግጭት መንስኤዎችን በጥናት ተደግፎ ይለያል፣ ግጭት እንዳይከሰት ይከላከላል፣ ሲከሰትም ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲፈታ ይጥራል፣ የተከሰቱ ግጭቶች ቢኖሩ ተዋናዩቹን የማረጋጋትና ማስተዳደር ሥራዎችን ያከናውናል፤

7) ወንጀል እንዳይፈፀም አስቀድሞ በመከላከል የክልሉን ህዝብ ሰላምና ደህንነት ያስጠብቃል፣ በወንጀል መከላከሉ ተግባር ላይም ህብረተሰቡ ንቁ-ተሳታፊ እንዲሆንና የራሱን ሰላምና ደህንነት እንዲጠብቅ ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

8) የህግ ታራሚዎች የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ በማያውክ ሁኔታ መጠበቃቸውን፣ በአግባቡ ታርመው ወደ ማህበራዊ ኑሮ መመለሳቸውንና ብቁ ዜጐች ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል፣ ለዚህም ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፤

9) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የህግ አስከባሪ አባላትና አመራሮች በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አያያዝና አጠባበቅ፣ በህገ-መንግስታዊና በወቅታዊ ጉዳዩች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት የህዝብ አገልጋይነት ሚናቸው እንዲዳብር ያደርጋል፤

4) Facilitate conditions whereby misunderstandings orising between and among the communities resident in the zonal, woreda and kebele administrations belonging to the regional state might be resolved peacefully and amicably;

5) Create favorable conditions for the pacific settlement of conflicts and misunderstandings arising between the region and its neighbouring states;

6) Identify the causes of conflicts having been supported by studies, prevent the occurrence of conflicts, strive to resolve same upon its emergence, using traditional and contemporary conflict resolvtion mechanisms and carry out the stabilization of actors and conflict management activities on account of those ongoing conflict;

7) See to it that the peace and security of the region's populace is safeguarded through an early prevention of the commission of crimes and encovrage the community so that the latter may participate in crime-prevention activities and hence-force take care of its own peacre security, as well as, extend the appropriate support thereof;

8) Follow up that prisoners of law are confined in such away as not to disrupt the peace and security of the community, are properly corrected and rehabilitated back to social life and released from detention as competent citizens , as well as, ensure that appropriate measures are taken to such an end;

9) Cause the enhancement of the role of law enforcement members and their leaderships belonging to the regional state in becoming public servants by building their capacity in the areas of handling and protection of human and democratic rights as well as constitutional and current issues of

importance;

10. የክልሉ የፀጥታ ተቋማት የሚመሩባቸውን የፖሊሲ ሀሣቦች፣ ህጎች፣ ስትራቴጅዎችና የአሰራር ስርዓቶች ያመነጫል፣ ያጠናል፣ የአፈፃፀም መርሀ-ግብሮችንና ስልቶችን ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የወጡ ህጎች በአግባቡ መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፤

10) Initiate and study the policy proposals, laws, strategies and working procedures in which the regional security institutions are to be directed, prepre the implementation programs and mechanisms and monitor the appropriate realization of laws issued thereof;

11. የፀጥታ ተቋማት ተልዕኳቸውን ለመፈጸም የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል፣ የትጥቅና የሌሎች አጋዥ ቁሣቁሶች ፍላጐት ያጠናል፣ በጥናቱ መሰረትም እንዲሟሉ ያደርጋል፤

11) Study the need of the security institutions for the necessary manpower, armament and other supporting materials with the view to accomplishing their mission and cause its fulfillment thereof as per the studies;

12. የትጥቅና የጦር መሣሪያ ግዥ ፍላጐቶችን ተመልክቶ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ግዥዎችን የመፈፀምና የመቆጣጠር ተግባራትን ያከናውናል፤

12) having looked into the armament and firearms purchasing requirements,, carry out the procurement and inspection activities in collaboration with the pertinent bodies;

13. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራሉ መንግሥት አካላት ጋር በመመካከር በህግ አግባብ ተደራጅተው በግል የደህንነት ጥበቃ ሥራ መሠማራት ለሚፈልጉ አካላት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ይቆጣጠራል፤

13) Issue and renew licese, delete and supervise same, in consultation with pertinent federal government organs, in respect of private security guard bodies organized by law;

14. በክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት በህግ በተሰጠው ሀላፊነት መሠረት የግል ደህንነት መጠበቂያ መሣሪያ ለሚያስፈልጋቸው ተቋማትና ግለሰቦች የማስታጠቅ፣ ፈቃድ የመስጠትና የማደስ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣ ህገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሮችን ይከታተላል፤

14) Supervise the undertaking activities of arming, licensing and renewing same in respect of those institutions and private persons qualifying to carry guns for self defense purposes pursuant to the law vested in power with the regional militia office and follow up illegal transfer of firearms;

15. በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታት፣ በህዝብ ደህንነትና በፀጥታ አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ አግባብ ካላቸው የፌደራል መንግስትና ከሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፣ ችግሮችን በጋራ ይፈታል፡፡

15) Maintain working relationships with the appropriate federal government and their bodies in matters involiving conflict prevention, management and resolution, as well as, public safety and security observance and thereby resolve problems in conjunction with them.

## 26.የባህልና ቱሪዝም ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉን ባህላዊ እሴቶች ያጠናል፣ መልካም የባህል ገፅታ እንዲዳብር ይጥራል፤

2) በክልሉ ውስጥ ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና መጤ ባህሎች እንዲወገዱና ጠቃሚ የባህል እሴቶች እንዲስፋፉ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ይሰራል፤

3) በክልሉ ውስጥ የባህል ቡድኖችና የኪነ-ጥበብም ሆነ የእደ-ጥበብ ክበባት እንዲደራጁና በባህሉም ሆነ በቱሪዝሙ ኢንዱስትሪ ልማት ገብተው በንቃት እንዲሳተፉ ያነሳሳል፣ ያበረታታል፤

4) በክልሉ ውስጥ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ በዘርፉ ለሚሰማሩ ወገኖች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

5) በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ ማህበር፣ የሐይማኖት ድርጅት ወይም ተቋም እጅ የሚገኙ ቅርሶች በሚገባ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፣ በኢግዚቪትነት የተያዙ ቅርሶችን፣ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ተቀብሎ አግባብነት ባለው መንገድ ያስተዳድራል፤

6) የክልሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋ፣ ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝና እንዲጠና፣ ቋንቋዎቻቸውም እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

## 26. The Culture and Tourism Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws , the culture and tourism bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Study the cultural values of the regional state and strive for the advancement of good cultural image thereof;
2) Work together with different governmental and non governmental organization by participating the society, the harmful traditional practices and the imported new cultures to be eradicated within the region;
3) Initiate the cultural groups and both art and artisan clubs to be organized and entering into both culure and tourism development to participate actively and encourage same in the region;
4) Cause the promotion of cultural institutions throughout the regional state; issue the certificate license of professional competence for those parties engaged in the sector , as well as, follow up and oversee their performance;
5) Provide support in favor of the proper handling and preservation of those heritages kept under the possession of any private person, association , religious organization or institution in the regional state, register and monitor same, as well as, receive and properly administer heritages wild animals and their products seized in the form of exhibits;
6) Cause the study, registration and preservation of the language, history and culture, as well as, the development and promotion of languages belonging to the nation-nationalities and people of the regional State;

7) በክልሉ ውስጥ ባህልና ቱሪዝም ነክ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፣ አስቀድመው በሚደረጉ የገበያ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ የክልሉን የቱሪስት መስህብ ሀብቶች በተለያዩ ዘዴዎች በማስተዋወቅ የአገር ውስጥና የውጭ ቱሪዝምን ያስፋፋል፤

8) በቱሪዝምና በመስተንግዶ እንዲሁም በጉዞና በአስጎብኝነት ሥራዎች የተሠማራው የሰው ሃይል ተገቢውን ሥልጠና የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያሰለጥናል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በክልሉ ውስጥ አኩሪ የቱሪዝም ባህል እንዲዳብር ያደርጋል፤

9) በፖርኮችና በሌሎች ጥብቅ ሥፍራዎች አካባቢ የሚገኘውን ህብረተሰብ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የቱሪዝም ዓይነቶችን ይለያል፣ እውቅና ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

10) በክልሉ ውስጥ ማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝም የሚያድግበትንና የሚጐለብትበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

11) ይህንን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣውን የአገልግሎት ዓይነት ስታንዳርድ መሠረት አድርጐ በክልሉ ውስጥ ለሚሰሩ የቱሪስት አገልግሎት ሠጭ ድርጅቶች ደረጃ ይሰጣል፣ ይህንኑ ደረጃ ጠብቀው ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ግዴታቸውን በማይወጡት ላይም የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

12) የቱሪስት ጉዞ መስመሮችና መመልከቻ ቦታዎች እንዲሠሩና እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና ሌሎች የአካባቢ ልማት እንቅስቃሴዎች ቱሪዝምን በሚደግፍ መንገድ ስለመካሄዳቸው ክትትል ያደርጋል፤

7) Collect, compile, analyse and transmit culture and tourism oriented data is the regional State and thereby promote domestic and foreign tourism by advertising the region's tourism attraction resources using various mechanisms, on the basis of prior marketing assessments;

8) Facilitate the conditions where by the human force engaged in the activities of tourism , entertainment, tour and travel agency might be provided with the appropriate trainings, render such training, follow up the implementation thereof and cause the enhancement of the tourism culture generating pride throughout the regional state;

9) Identify, accord due recognition and register the types of tourism enabling the community settling around the parks and other protected places to directly benefit there from and henceforth facilitate the conditions of their further development;

10) Facilitate conditions in which community centered tourism might be developed and strengthened;

11) Having recourse to the standards to be set issued following this proclamation as per the types of such services, issue grades to the tourist service, delivering enterprises in the regional state , monitor and supervise over their performance in compliance with the requirements of these grades, as well as, take of cause administrative actions to be taken against those failing to discharge their duties;

12) Cause the construction and organization of tourist travel routes and spectacular sits and follow up, in collaboration with the relevant bodies, that the infrastructural building and local development activities in the regional state are undertaken in such a way as to support tourism;

13) አግባብ ካላቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር በብሔራዊ ቅርሶች፣ በፖርኮች፣ ለአደን በተከለሉ አካባቢዎችና የዱር እንስሳት መጠለያ ሥፍራዎች ውስጥ የሰፈረው ነዋሪ ህዝብ ራሱ በሚሳተፍበትና የመፍትሔው አካል ሆኖ በሚቀርብበት አኳኃን ወደ ሌላ አካባቢ ሊዛወር የሚችልበትን ስልት ይቀይሳል፤

14) በክልሉ ውስጥ በቱሪስት አገልግሎት፣ በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ንግድ ለሚሠማሩ ድርጅቶች፣ ተቋማትና ግለሰቦች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ይደግፋል፣ በንግድ ሥራም ሆነ በሌላ ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ ለሚንቀሳቀሱ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው መነሻና መድረሻቸውን የሚያመላክት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

15) በክልሉ ውስጥ ከፖርኮችና ጥብቅ ሥፍራዎች ውጭ የሚገኙትን የዱር እንስሳት ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በትብብ ይሰራል፡፡

## 27. <u>የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የሴቶችንና የህፃናትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ ሃሣቦችን ያመነጫል፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

13) In collaboration with the appropriate regional state bodies, devise a mechanism through which the community inhabiting inside the national heritage sits, parks, areas reserved for hunting purposes and sanctuaries of wild animals, may be transferred into another settlement in such a way as to invole its own participation and being presented as constituting part of the solution thereof;

14) Issue crrtificate of professional competence to and support those organizations, institutions and individuals trading with tourist services, as well as, wild animals and their products throughout the regional state and render authorizations indicatve of origin and destination in respect of wild animals and their products during mobility from place to place, be it for business of other purposes;

15) Work with cooperation together with appropriate bodies that the security of wild animals, those are found out of the parks and preserved places, to be protected in the region.

## 27. <u>The Women and Children Affairs Bureau</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the women and children affairs bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

**1)** Initiate proposals with the view to enforcing the right and interests of women and children in the regional state, as well as, devise implementation strategies and carry out the necessary follow ups;

2) በክልሉ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጐች፣ የልማት ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ሪፖርቶች የስርዓተ ጾታን ጉዳይ ለማካተት የሚያስችላቸውን ስልት በመንደፍ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ በሂደትም የሴቶችን ተሣትፎና ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፤

3) ሴቶች በክልሉ የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው ሥለመሆኑ በቅርብ ይከታተላል፤

4) በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚቃጡ መድሎዎችንና የሚፈፀሙ ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት እነዚሁ የሚወገዱባቸውን የመፍትሄ ሃሣቦች ያመነጫል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

5) ሴቶች ለዘመናት በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ተሣትፏቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ለክልሉ መንግሥት ሃሣብ ያቀርባል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

6) የተለያዩ የክልሉ መንግስት አካላት ሴቶችን በውሣኔ ሰጭነት ቦታዎች በመመደቡ ረገድ በቂ ትኩረት ስለመስጠታቸው ይከታተላል፤

7) ሴቶች እንደፍላጎታቸውና እንደየችግሮቻቸው አይነት ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

8) ብሄራዊው የሴቶች ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን የሚደረጉ ጥረቶችን ያስተባብራል፤

2) Provide the necessary follow up and support for the regional government bodies in the course of their preparation of policies , laws, development programs, projects and reports by having formulated a mechanism enabling them to mainstream gender issues and thereby ensure the participation and entitlement of women in such process;

3) Follow up closely that opportunities are facilitated for women to actively participate in the region's political, economic and social endeavors;

4) Identify , in the course of studies , those discriminatory and harmful traditional practices directed against women and children, propose recommendations for their elimination and thereby follow up the implementation of same;

5) Propose to the regional government as to the creation of favorable conditions in which to give special attention ans support for women with the view to increasing their participation in economic, social and political activities , taking into account the domination they have suffered from due to their treatment, for ages, with inferiority and discrimination and follow up its implementation thereof;

6) Monitor that the various regional government bodies pay sufficient attention as regards the assignment of women is decision making positions;

7) Encourage and facilitate an enabling condition for women to struggle for the enforcement of their rights and interests and thereby eliminate their difficulities, having organized themselves on account of their specific needs and kinds of problems;\

8) Coordinate the efforts undertaken to implement the national women's policy within the limit of the regional State;

9) በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በዚሁ ዓላማ ላይ ተመስርተው ለሚንቀሳቀሡ ድርጅቶችም አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

10) ስርዓተ--ጾታን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከተለያዩ የማህበረሰብ ተቋማትና ከራሣቸው ከሴቶች ማህበራት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

11) የጾታ እኩልነትን ለማስፈን፣ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን ተሣትፎ ለማጎልበትና ህብረተሰቡ በሴቶች ላይ ያለውን የተሣሣተ ግንዛቤ ለመቀየር የሚረዱ ስልጠናዎችንና ዓውደ-ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ውጤቶታቸውንም ይገመግማል፤

12) ሴቶች በክልሉ ውስጥ በሚሰጡ የስራ ቅጥር፣ የስልጠናና የደረጃ እድገት እድሎችም ሆነ እነዚህኑ ለማስፈፀም በሚደራጁ የተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በሚገባ ስለመወከላቸው ይከታተላል፤

13) ሴቶችን ለሚያግዙና ለክልሉ ዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ሀብት ያፈላልጋል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆንም ድጋፉ የክልሉን ሴቶች ህይወት ለማሻሻል ስለመዋሉና ውጤታማ ስለመሆኑ ይከታተላል፤

14) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብ እና የህፃናት ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግና የጋብቻ ስርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

9) Carry out studies or cause same to be carried out with the view to assisting women found in low standard of life, improve their livelihoods, formulate and implement programs and projects; and provide the necessary support for those organizations established and acting upon such purpose;

10) Work in collaboration with the non-governmental organizations, various communal institutions and the associations of women themselves, on matters relating to gender;

11) Undertake trainings and workshops bound to assist the realization of gender equality , enhancement of women's participation in various activities, as well as, correction of the misperception of the community regarding women and thereby evaluate the result thereof;

12) Follow up that women are duly represented in an employment, training and promotion opportunities provided in the regional state and in the various committees to be established for the execution of same;

13) Search for a resource to be utilized for the execution of projects likely to assist women and contribute for the region's sustainable development, as well as, follow up in collaboration with the relevant bodies, that the support is employed to improve the living conditions of women in an effective way;

14) Implement in cooperation with the relevant bodies, policies issued for the protection of the family and children, as well as, marriage institutions;

## 28. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎችና ህጐች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
2) አሠሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
3) የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
4) በብሔራዊ ክልሉ የግዛት ወሰን በየድርጅቱ የሚቋቋሙትን የሠራተኛና አሰሪ ማህበራት ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
5) የህብረት ስምምነት ድርድሮችና የሥራ ክርክሮች በህግ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍፃሜ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፣ የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤
6) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለሙያው አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፤
7) በክልሉ ውስጥ ሥራ ፈላጊዎችና ክፍት የሥራ መደቦች እንዲመዘገቡና ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኝ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

## 28. The Labor and Social Affairs Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the labor and social affairs bureau shall, pursuant to this proclamation, have the the following particular powers and duties:

1) Cause the implementation of the country's policy of labor and social affairs in the region;
2) Ensure that laws , regulations and directives issued concerning employers and workers are respected with in the region;
3) Supervise over the implementation of labor conditions standards and protective devises issued for maintaining employees, safety and health;
4) Register workers and employers associatins with in the administrative boundary of the national region, and provide support thereto;
5) Make the necessary effort for the efficient settlement, following the procedures established by law of collective agreements of negotiations and trade disputes; and register collective agreements;
6) Undertake studies in cooperation with the relevant bodies, concerning the manpower of the region and occupational classification of same;
7) Take measures to enable the proper registration of job seekers and vacancies, and exchange of labor and employees in the region;

8) ስለክልሉ የሰው ኃይልና የሥራ ስምሪት፣ ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤና እንዲሁም አሰሪና ሠራተኛን ስለሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ከትንተና ጋር ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤

9) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን አረጋዊያንንና አካል ጉዳተኞች ለመደገፍና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

10) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በስራ ላይ ያሉትን የአረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ፣ ተሀድሶና እንክብካቤ ማዕከላት ያስተዳድራል፣ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች እንደተገቢነታቸው መሰል ማዕከላትንና ድርጅቶችን ያቋቁማል፤

11) የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ይወገዱ ዘንድ የክልሉን ህብረተሰብ ሁለንተናዊ ጥረት ያስተባብራል፣ በአስከፊ ችግር ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

## 29. <u>የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉን ዘላቂ የልማት አቅጣጫዎች መሠረት አድርጎ በየጊዜው የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን በማጥናት ይለያል፣ ክፍተቶቹም እንዲሞሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤



8) Collect, compile, analyse and transfer to the concerned bodies information pertaining to manpower and employment, safety and health of workers, as well as, other matters related to employer and workers in the region;

9) Prepare programs enabling the assistance and rehabilitation of the elders and the handicaped in the region; and upon approval, implement same;

10) Administer the elders and disabled persons support, rehabilitation and care centers in effect, being the particular determined with issued regulation to execute this proclamation; and establish similar centers and organizations as proper, by different places of the region;

11) Coordinate an overall effort of the society of the region to be eradicated the livelihood of social faults; work with cooperation with the pertinent bodies of the issue to get different services of the parts of the society who have been found in serious problem.

## 29) <u>**The Civil Service and Human Resource Development Bureau**</u>

Without prejudice to the existing or sebsequennt provisions of other laws, the civil service and human resource development bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Study and identify the capacity gaps encountered over the time , having due regard to the sustainable development directions of the regional state and thereby facilitate conditions for the filling of such

gaps;

2) ለክልሉ ሁለንተናዊ ልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መፋጠን የሚረዱ ልዩ ልዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ ሁኔታ መቀረፃቸውን ፣መከለሳቸውንና መተግባራቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

3) በክልሉ ውስጥ የተለያዩ የለውጥ ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አጠቃላይ የክትትል፣ የግምገማና የድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት ይዘረጋል፣ ይኸው በሥራ ላይ እንዲውል የክልሉን መንግሥት መስሪያ ቤቶች ያማክራል፤

4) ለክልሉ ዘላቂ እድገት እርባና ያላቸው አዳዲስ ተቋማት በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲቋቋሙና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነባሮቹ እንደገና እንዲደራጁ፣ በአሠራር እንዲጠናከሩና በተገቢው መንገድ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የውሣኔ ሀሣብ ያቀርባል፤

5) የክልሉን ህዝብ መንግስታዊ አገልግሎት አስመልክቶ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችንና ደንቦችን ያመነጫል፣ የደመወዝ ስኬልና ልዩ ልዩ አበሎችን እንዲሁም የክልሉን የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ውጤት መመዘኛ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

6) በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ዘመናዊና የተሟላ የሰብአዊ ሀብት አመራር ትምህርት፣ ሥልጠና፣ ልማትና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱንና በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

2) Follow up and support over the formulation, revision and implementation of the reform programs and projects assisting to accelerate the overall development and building up of the democratic order in the regional state;

3) Put in place a comprehensive monitoring, evaluation and support-provision system enabling to effectuate the realization of the various change programs throughout the regional state and ascertain its implementation thereof;

4) Cause the establishment, on the basis of initial studies of the new institutions where necessary, the reorganization, consolidation in working procedures and standardized operation of the existing ones bound to have significance for the region's sustainable development;

5) Regarding public service of the regional people, initiate policies, laws and regulations; prepare and upon approval, follow up the implementation of salary scales and various allowances, as well as , performance evalution criteria applicable to the region's civil servants;

6) Follow up and support the creation and implementation, in the regional civil service of a modern and complete human resource management eduction , training, development and utilization thereof;

7) የክልሉን መንግሥት ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል፣ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ውጤታማና ብቃት ያለው የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በተለያዩ የሰው ኃይል ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፤

8) በክልሉ ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ መታገድ፣ በከባድ የዲስፒሊን ቅጣት ከህግ ውጭ በደመወዝ መያዝ ወይም መቋረጥ፣ በሥራ ምክንያት በደረሰ ጉዳት ሳቢያ የመብት መጓደል ሲያጋጥም ወይም የስራ መልቀቂያንና የአገልግሎት ማስረጃን አስመልክቶ በተወሰደ እርምጃ የሚቀርቡለትን ይግባኞች በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አማካኝነት በመመርመር የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል።

## 30. የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ወጣቶችን በተመለከተ የወጡ አገር አቀፍ ፖሊሲዎች፣ ፖኬጆችና ስትራቴጅዎች በአግባቡ ሠርፀው በክልሉ ውስጥ እንዲፈፀሙ ይሰራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

2) ወጣቶችን ማዕከል አድርገው የሚሰሩ የተለያዩ አካላትን የተግባር ዕቅድና አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖራቸው ያስተባብራል፤

7) Record and mainatain the particulars of the region’s civil servants, compile the statistical information, put in place an effective and efficient information system and carry out studies and researches in various issues pertaining to human resource;

8) Entertain and render final decisions on appeals with regard to administrative tribunal submitted to it by the region’s civil servants, due to the infringement of rights, as the result of suspension from duty, rigorous disciplinary penalities, unlawful withholding or termination of salary, or where exists unsufficient rights or with measures taken concerning to clearance and evidence of service.

## 30. The Youths and Sport Affairs Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the regional youths and sport affairs bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and dities:

1. Work for, follow up, coordinate and oversee the proper internalization and execution of those policies, packages and strategies nationally issued as regards the youths, throughout the regional state;
2. Follow up, supervise and coordinate the integrated operation of the action plans and implementation of the various actors focusing on the youths;

3) የክልሉ ወጣቶች በነፃ ፍላጐታቸው ተደራጅተው በክልሉና በሀገሪቱ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ መልካም አስተዳደርና የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅም እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ በየተቋቋሙበት አግባብ ተግባራቸውን እየተወጡ ስለመሆኑም በቅርብ ይከታተላል፤

4) የክልሉ ወጣቶች የክልሉንና የአገሪቱን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህልና ታሪክ እንዲያውቁ የሚያስችሉ የወጣቶች የንቅናቄና የተሳትፎ መድረኮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ሥራዉን በበላይነት ያስተባብራል፤

5) የክልሉን ወጣት-ነክ መሠረታዊ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሠራጫል፣ ወጣት ተኮር የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

6) ክልላዊ የስልጠና ስታንዳርዶችንና የአቅም ግንባታ ፖኬጆችን እያዘጋጀ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለወጣቶች ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

7) ስፖርትን በተመለከተ የወጡ አገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች በአግባቡ ሠርፀው በክልሉ ውስጥ እንዲተገበሩ ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

8) የክልሉን ስፖርት እድገት እውን የሚያደርጉ ረቂቅ ህጐችንና ደንቦችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

3) provide universal support to the region's youth so that they would participate with full capacity in the building up of the democratic order, good governance and development efforts both at the regional and national levels and benefit there from, as well as, monitor that they discharge their respective duties pursuant to the terms of their establishment;

4) cause the preparation of the youth participation and movement forums enabling the youth of the regional state to know the culture and history of the nationalities and peoples inhabiting the region and the country at large and coordinate the activities from above;

5) collect and organize basic information in relation to the youth, transmit same to the relevant bodies, as well as, cause the undertaking of youth focused study and research activities;

6) having prepared regional training standards and capacity building packages for youths ' cause the provision of trainings , in collaboration with the educational institutions and follow up the implementation of same thereof;

7) work for , follow up, coordinate and oversee the proper internalization and execution of those policies and strategies nationally issued regarding to sports, throughout the region;

8) prepare draft laws and regulations, necessary to realize the development of sport of the reagion, and thereby present to the concerning bodies to be promulgated; follow up and oversee the execution of same;

9) በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ስፖርቶች ሊስፋፉ የሚችሉባቸውን አካባቢዎች ወይም ለስፖርቱ እድገት የሚውሉትን የተፈጥሮ ጸጋዎች በመለየት በልዩ ሁኔታ የስፖርት ፕሮጀክቶችንና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

10) በክልሉ ውስጥ ለሚገነቡት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የስልጠና ማዕከላት ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በየደረጃው እንዲገነቡና አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣ የህግ ከለላ እንዲኖራቸው ድጋፍ ይሰጣል፤

11) የክልሉን ስፖርት ነክ መሠረታዊ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሠራጫል፣ ለስፖርቱ ልማት ዘርፍ የሚጠቅሙ የጥናትና የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

12) በስፖርቱ የልማት ዘርፍ የተሰማራውን ሙያተኛ አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ የረዥምና የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን ያመቻቻል፤

13) የስፖርት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሠጭ ወጣቶችን በስፋት በማደራጀትና በማቋቋም ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋል፤

14) ህብረተሰብ አቀፍ የስፖርት ተሣትፎ ፕሮግራም ወይም ፖኬጅ በማዘጋጀት ማህበረሰቡ በሚኖርበት፣ በሚሠራበትም ሆነ በሚማርበት አካባቢ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተሣታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤



9) Establish in a special circumstance, projects and institutions of sport; by identifying areas where different sports to be expanded or the natural potentials applied to the development of same in the region; and provide the proper support and follw up thereof;

10) Prepare standards for gymnasiums and traninig centers throughout the region, cause such facilities to be constructed and render service at various levels, and give support to get legal protections;

11) Collect and organize basic information in relation to sport in the region, and transmit same to the relevant bodies; and cause study and research activities, important for the sport development sector, to be conducted thereon;

12) Facilitate long and short term training to strengthen the capacity of professionals working in sport development sector;

13) Organize and establish widely youths rendering voluntary sport services and thereby cause them to highly contribute to the sector

14) Having prepared the mass sport pariticipation programs or packages, cause the people participate in and hence forth benefit from sport activities in their habitat, working and learning environment;

15) የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም የስፖርት ገቢዎችን ያሰባስባል፣ ለታለመላቸው ዓላማ ያውላል፣ የስፖርት ማህበራት የሚሰበስቡት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፤

16) በክልሉ ውስጥ በስፖርት ኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ ባለሃብቶች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በስታንዳርዱ መሠረት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

17) አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር በወጣት ማእከላት፣ በታላላቅ ሆቴሎች፣ ሪል-ስቴቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶችና በመሣሠሉት ሌሎች አካባቢዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥሪያ ቦታዎች ተካተው መሠራታቸውን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

18) ስፖርት ለስራ ፈጠራ የሚኖረው ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት በሽያጭና በዝውውር አማካኝነት በክለቦች የሚታቀፉ ስፖርተኞች የጉልበት ብዝበዛ እንዳይደርስባቸው ይከታተላል፣ የስልጠና ማዕከል ከፍተው የራሣቸውን ስራ ለሚፈጥሩ አካላት ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

19) በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት ስታንዳርድ ያወጣል፣ በስታንዳርዱ መሠረት ያቋቁማል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሥራ ውል ይይዛል፣ ፕሮግራማቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

15) Collect, using various revenue –raising mechanisms, sport incomes and employ same for the intended purpose, as well as, audit and supervise the accounts of the sports' association in an effort to ascertain that the revenue they may have collected is utilized only for the accomplishment of their purposes;

16) Prepare standards for investors wishing to engage themselves in sport investment in the region; issue and supervise professional license in line with such standards thereof;

17) Follow up and render support to, in consulation with the pertinent bodies, the accommodative use of physical exercise undertaking sites within the premise of youth centers, grand hotels, realstates, hospitals, schools and other similar institutions;

18) Follow up , considering the importance of sport to invention of work, to sportsmen and women embraced in clubs to be protected from labour exploitation due to sales and transfer; provide appropriate support for bodies who open their own work through opening training center;

19) Issue standards to the establishment of sport associations at various levels in the region; cause same to be established as per such standards; issue license, enter ito working contracts; coordinate and supervise the programs of same thereof;

20) በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የስፖርት ም/ቤቶች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

21) በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር በስፖርታዊ ችግሮች ዙሪያ ጥናቶችና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ በተገኘው ውጤት መሠረትም ተፈፃሚ ያደርጋል፤

22) ክልላዊ የስልጠና ስታንዳርዶችንና የአቅም ግንባታ ፖኬጆችን በማዘጋጀት ከክልሉ ትምህርት ቢሮ እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለስፖርት አመራሮችና ባለሙያዎች፣ ለአሰልጣኞችና ለስፖርተኞች ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

23) የክልሉን ስፖርታዊ ውድድሮች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ውድድሮችን ያካሂዳል፣ ውድድር እንዲያዘጋጁም ተገቢውን ፈቃድ ይሰጣል፤

24) ክልላዊ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማህበራትና በሌሎች አካላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሣኔ ይሰጣል፤

25) በክልሉ ውስጥ ባህላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁና የራሣቸው ሕግና ደንብ የሌላቸውም ይኸው እንዲወጣላቸው ይሠራል፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

20) Cause the establishment and strengthening of the sports' councils at various levels in the region;

21) Carry out studies in relation to problems of sport in collaboration with higher educational institutions in the region; and thereby implement as per the outcome of the same;

22) Cause the provision of trainings, in collaboration with education bureau of the region and higher educational institutions, for leaders and professionals of sport, for coaches and sportsmen and women upon the preparation of regional training standards and capacity building packages; follow up the implementation of same thereof;

23) Prepare standard for the regional sport competitions; undertake sport competitions in collaboration with relevant bodies; and issue license for those wishing to undertake same;

24) Adjudicate disagreements that may arise among sport associatins and other bodies in relation to regional sport competitions and thereby render administrative decisions;

25) Work for the popularization of traditional sports and the issuance of laws and regulations devoid of same in the region; encourage and provide support to the improvement and growth thereof;

26) ከህብረተሰቡ አቅም ጋር የተገናዘቡ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች በክልሉ ውስጥ የሚመረቱበትንና ከሐገር ውስጥም ሆነ ከውጪ በድጋፍ መልክ የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

27) ስፖርትን በማስፋፋትና በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ የስፖርት ማህበረሰቦች፣ ግለሰቦች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግልፅ መመሪያ በማዘጋጀት የማበረታቻ ሽልማቶችን ይሠጣል፣ ለበለጠ ሥራ ያነሳሳል፤

28) ከክልሉ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲና ሌሎች የሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የአካል ብቃት እንቅስቃሴና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን እንዲተላለፉ በቅርብ ይሰራል፤

29) ከክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመተባበር ከስፖርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጤና ነክ ጉዳዮች በእቅድ አካቶ ይሰራል፡፡

31. <u>ስለ ሌሎች የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት</u>

1) የብሔራዊ ክልሉ መንግስት ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በየተቋቋሙባቸው ህጐች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፤

2) የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት በቀጥታ ለብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ተጠሪዎች ይሆናሉ፡-

ሀ/ የአመራር አካዳሚ፤

ለ/ የገቢዎች ባለስልጣን፤

26) Facilitate condition whereby sport equipment and instruments be produced in the region; and their availability from domestic and external sources in the from of support;

27) Hand over awards to, upon the preparation of clear directives, sport societies, individuals, civic associations, governmental and non – governmental organizations for their high contribution to the promotion and development of sport; and thereby motivate for additional work;

28) Work closely, in collaboration with the mass media agency of the region and other media organizations, for the transmission of important physical exercises and awareness creation educations through radio and on television;

29) Implement health related issues to sport with a prior plan in collaboration with bureau of health of the region.

31. **<u>Other Executive Bodies of the Regional State</u>**

1) Other executive bodies of the national regional state shall run on their activities as provided by their respective establishment laws;

2) The following executive bodies shall be accountable directly to the Head of Government of the National Reginal State:

a/ the leadership academy;

b/ the Revenue's authority;

ሐ/ የአካባቢ፣ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ባለስልጣን፤

መ/ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

ሠ/ የፕላን ኮሚሽን፤

ረ/ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጅና ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ኮሚሽን፤

ሰ/ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፡፡

3/ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ግብርና ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ/ የዘርና የሌሎች ግብርና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥርና የኳራንታይን ባለስልጣን፤

ለ/ የግብርና ምርምር ተቋም፤

ሐ/ የእንስሳት ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፤

መ/ የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፤

ሠ/ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፡፡

4) የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ/ የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፤

ለ/ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ኤጀንሲ፡፡

5) የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ/ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት፤

c/ the Environment, forest and Wild lives protection and Development authority;

d/ the investment commission;

e/ the plan commission;

f/ the Science, Technology and Information Communication Commission;

g/ the Government Communication Affairs Office.

3/ The following executive bodies shall be accountable to the Regional Bureau of Agriculture:

a/ the seed and other agricultural inputs quality control and quarantine authority;

b/ the Agricultural Research Institute;

c/ the Animals Resource Development Promotion Agency;

d/ the cooperative societies promotion Agency;

e/ the disaster prevention and food security program coordination Office .

4) The following executive bodies shall be accountable to the Regional Techinc-Vocation and Enterprises Development Bureau:

a/ the Mines Resource Development promotion agency;

b/ certificate of professional competence agency.

5) the following executive bodies shall be accountable to the Regional Justice Bureau:

a/ the Justice professionals Training and Legal Research Institute;

ለ/ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ፡፡

6) የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ/የፖሊስ ኮሚሽን፤

ለ/ የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፤

ሐ/ የሚሊሻ ጽ/ቤት፡፡

7) የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ/ የሙሉአለም ባህል ማዕከል፤

ለ/ የሰማዕታት ሀውልት ጽ/ቤት፡፡

8) የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለክልሉ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ይሆናል፤

9) የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ተጠሪነት ለክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ይሆናል፤

10) የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም ጽ/ቤት ተጠሪነት ለክልሉ ውሀ፣መስኖና ኤነርጅ ልማት ቢሮ ይሆናል

11)የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጠሪነት ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ይሆናል፡፡

32. **<u>አስፈፃሚ አካላት በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆናቸው</u>**

1) በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሆኑ አስፈፃሚ አካላት በክልሉ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ በየዞኑ መምሪያዎቻቸውን ወይም ተጠሪ ጽ/ቤቶቻቸውን ሊያደራጁ ይችላሉ፤

b/ the vital events registration agency

6) the following executive bodies shall be accountable to the Administration and security affairs Bureau:

a/ the police commission;

b/ the prisons commission;

c/ the Militia office.

7) the following executive bodies shall be accountable to the Regional Culture and Tourism Bureau:

a/ the Mulualem Cultural Center;

b/ the Martyrs Monument Office.

8) The Urban Plan Institute shall be accountable to the Regional Urban Development, Houses and Construction Bureau;

9) The Rural Roads construction agency shall be accountabler to the Regional Road and Transport Bureau;

10) The kobo Girana valley Development program office shall be accountable to the Regional water, Irrigation and Energy Development Bureau;

11) The Governmental procurement and property eradication service shall be accountable to the Regional Finance and Economy Collaboration Bureau;

32. **<u>Establishment of Executive Bodies at all Levels</u>**

1) Executive bodies , which have been established as per this proclamation and members of the council of the regional government, may as deemed as necessary , organize offices or departments, accountable thereto in each zone throughout the regional state;

2) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብሄረሠብና የወረዳ አስተዳደሮች በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ቀጣይነት ላለው ልማትና ለተፋጠነ አገልግሎት አስፈላጊ ሆነው የሚያገኟቸውን የአስፈፃሚ አካላት መምሪያዎችንና ዋና ጽ/ቤቶችን የማቋቋም መብት ይኖራቸዋል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /2/ በተደነገገው መሠረት የብሄረሰብና የወረዳ አስተዳደሮች መንግስታዊ ተቋማትን ለማደራጀት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚያቀርቡትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ አግባብ ያላቸው የብሄራዊ ክልሉ አስፈፃሚ አካላት ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 33. ስለ ተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

1) የሚከተሉት ህጐች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ/ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም / እንደተሻሻለ/፤

ለ/ አዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ምን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 222/2007 ዓ.ም፤

ሐ/ የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ማስፋፊያ ቢሮን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 205/2005 ዓ.ም፤

2) The Nationality and Woreda Administrations in the region shall, by virtue of the powers vested in them pursuant to the Revised Constitution of the National Regional State, have the right to establish executive departments and direct over offices that are found to be necessary for sustainable development and rapid service delivery thereof;

3) The relevant executive organs of the National Regional State shall, pursuant to sub-article/2/ of this Article hereof, have the responsibility to provide appropriate support to the nationality and woreda administrations in their activities of organizing governmental institutions, upon request for same.

## PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 33. Repealed and Inapplicable Laws

1) The following laws are repealed by this proclamation:

a/ the Amhara National Regional State Executive Organs Establishment and Determination of their Powers and Duties proclamation No 176/2011 /as amended/;

b/ the issued proclammation No 222/2014 to amend the proclamation No 176/2011;

c/ a proclamation issued to provide for the establishment and determination of powers and duties of the technic-vocation and Enterprises development Expansion Bureau of proclamation No. 205/2013;

መ/ የክልሉን ንግድ ቢሮ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 218/2006 ዓ.ም፤

ሠ/ የክልሉን ትራንስፖርት ባለስልጣን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 219/2006 ዓ.ም፤

ረ/ የክልሉን ስፖርት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 177/2003 ዓ.ም፤

ሰ/ የክልሉን የማዕድንና የገጠር ኢነርጅ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም/ እንደተሻሻለ/፤

ሸ/ የክልሉን ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 202/2005 ዓ.ም፤

ቀ/ የክልሉን የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ ልማት ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣው ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 72/2002 ዓ.ም/ እንደተሻሻለ/።

2) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 34. <u>መብቶችና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>

1) ኢንዱስትሪ ነክ ጉዳዩችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲሁም ንግድ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 218/2006 ዓ.ም ለንግድ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤



d/ the issued proclamation N<u>o.</u> 218/2014 to provide for the regional trade bureau;

e/ the issued proclamation N<u>o</u> 219/2014 to provide for the regional transport authority;

f/ the issued proclamtion N<u>o.</u> 177/2010 to provide for the regional sport commission;

g/ the issued proclamation N<u>o.</u> 100/2004 ( as ammended) to proide for the regional Mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office;

h/ the issued proclamation N<u>o.</u>202/2013 to provide for the regional rural roads authority;

i/ the issued regional government council regulation N<u>o.</u> 72/2009 ( as amended) to provide for the regional information communication technology development agency.

2) Any law, regulation, directives or customary practice inconsistent with this proclamation , may not apply to matters provided for therein;

## 34. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>

1) the rendered rights and obligations to the regional Industry and urban Development Bureau with proclamation N<u>o</u> 176/2011 concerning to industrial issues, as well as, to the trade Bureau with proclamation N<u>o</u> 218/2014 concerning to trade issues have been transferred to the newly established regional Trade, Industry and Market Development Bureau, pursuant to this proclamation;

2) የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ጉዳዮችን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም መሠረት ለኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ተላልፈዋል፤

3) የውሀ ሀብትና የመስኖ ልማት ጉዳዮችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም ለውሀ ሀብት ልማት ቢሮና እንዲሁም የኢነርጅ ጉዳዩችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ መሠረት ለማዕድንና የገጠር ኢነርጅ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ ውሀ፣መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤

4) በአዋጅ ቁጥር 73/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ መሠረት ለክልሉ ኤች አይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ሴክሬታሪያት ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ወደ ተቋቋመው የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ተላልፈዋል፤

5) የመንገዶች ግንባታና ጥገናን ሣይጨምር በአዋጅ ቁጥር 202/2005 ዓ.ም መሠረት ለገጠር መንገዶች ባለስልጣንና በአዋጅ ቁጥር 219/2006 ዓ.ም መሠረት ለትራንስፖርት ባለስልጣን ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፤



2) The rendered rights and obligations to the Industry and Urban Development Bureau with procalamation No. 176/2011, concerning to the urban development, houses and construction issues have been transferred to the newly established regional urban development, houses and construction Bureau;

3) The rendered rights and obligations to the water resource development bureau with proclamation No. 176/2011 concerning to the water resource and irrigation development issues, as well as, to the mines and Rural Energy Resource Development Expansion Agency with proclamation No. 100/2004 (as ammended) concerning to the energy issues have been transferred to the newly established regional water, irrigation and energy development bureau, pursuant to this proclamation;

4) The rendered rights and obligations to the regional HIV/AIDS prevention and control secretariat Council with proclamation No. 73/2002(a) amended have been transferred to the newlly established Health Bureau of the Region, pursuant to this proclamation;

5) The rendered rights and obligations to the Rural Roads Authority with proclamation No.202/2013 excluding the roads construction and maintenance service and to the Ttransport Authority with proclamation No. 219/2014 have been transferred to the newly established Roads and Transport Bureau of the Region, pursuant to this proclamation;

6) በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም መሠረት /ፓርኮችን ሳይጨምር/ ለክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተላልፈዋል፤

7) ሴቶችና ህፃናትን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም መሠረት ለሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ተላልፈዋል፤

8) ወጣቶችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም መሠረት ለሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ እንዲሁም ስፖርትን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 177/2003 ዓ.ም መሠረት ለስፖርት ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

## 35.አስፈፃሚ አካላትን ስለማደራጀት

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የብሔራዊ ክልሉን አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት አስመልክቶ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ለውጦችን ከማድረግ ባሻገር አዳዲስ ተቋማትን የመመስረት፣ ተግባርና ሀላፊነታቸውን የመወሰን አንደኛውን ከሌላው ጋር የማዋሀድ እንዲሁም በህግ መሰረት ስልጣንና ተግባራቸውን የማንሳት ተግባራትን እንዲያከናውን በዚህ አዋጅ ከህግ-አውጭው ምክር ቤት የውክልና ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

6) The rendered rights and obligations to the Culture, Tourism and Parks Development Bureau with the proclamation No. 176/2011 (excluding parks) have been transferred to the newly established culture and tourism bureau of the Region, pursuant to this proclamation;

7) The rendered rights and obligations to women, children and youths affairs bureau with proclamation No.176/201 concening to women and children have been transferred to the newly established women and children affairs bureau of the region, pursuant to this proclamation;

8) The rendered rights and obligations to women, children and youths affairs bureau with proclamation No. 176/2011, concerning to youths, as well as, to the sport commission with proclamation No. 177/2010 concerning to sport have been transferred to the newly established youths and sport affairs bureau of the region, pursuant to this proclamation.

## 35. Organizing Executive Bodies

The council of the Regional Government , with regard to the organization of executive bodies of the National Regional State, is apart from introducing changes on the basis of studies , hereby authorized through delegation on the part of the legislative council, pursuant to this proclamation to carry out such activities as the establishment of new institutions, determination of their respective duties and responsibilities , integrating one with the other , as well as, revoke their powers and duties inaccordance with law.

## 36. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ ተቋቁመው የነበሩና በዚህ አዋጅ መሠረት ወደተደራጁት ቢሮዎች ያልተጠቃለሉ የሥራ ዘርፎች በሌሎች ህጎች ወደፊት በሚቋቋሙ አዳዲስ አስፈፃሚ አካላት እስከሚያዙ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በተደራጁትና ለሥራው ቀደምት ባለቤቶች በነበሩ ቢሮዎች አማካኝነት መከናወናቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ሆኖም አዋጁ በዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከ3 ወር በኃላ የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይቋረጣል፡፡

## 37. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 38. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የብሄራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይህንን አዋጅ ተከትለው የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስችሉ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 39. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**
**ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም**
**ገዱ አንዳርጋቸው**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት**

## 36. Transitional Provisions

Those sets of activities which were the mandates of those executive organs established under proclamation No. 176/2011, and not transferred to the bureaus reorganized, pursuant to this proclamation shall continue being carrid out by these bureaus, having become their prior mandate holders, until such time that they shall have been taken over by their respective new bodies to be established by other laws.

## 37. Power to Issue Regulations

The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the full implementation of this proclamation provisions.

## 38. Power to Issue Directives

The Head of the Government of the National Regional State may issue particular directives enabling to execute the regulations to be issued following this proclamation.

## 39. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its official publication on the Zikre-Hig Gazzeettee of the Regional State.

**Done at Bahir Dar,**
**This 3rd Day of February, 2016**
**Gedu Andargachew**
**President of the Amhara National Region**